ማውጫ


ገጽ

መግቢያ ...... 3

ክፍል አንድ

የእግዚአብሔር ፍቅር ...... 5

ክፍል ሁለት

ክርስቶስን በመከተል በሃይማኖት መገለጥ ...... 8

2.1.የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ የሚባሉት ምንድን ናቸው? ...... 9

2.2.በሃይማኖት መቆም ምን ማለት ነው? ...... 9

2.3.መንፈሳዊ ምግባርና ሕይወት ምን ምን ከማድረግ ይነሣል? ...... 10

ክፍል ሦስት

የጸሎት ቤት ...... 10

3.1 በክርስትና ዕለት ዕለት እንዴት መኖር እንችላለን? ...... 11

3.2 በክርስትና ዕለት ዕለት ለመኖር ምን ከማድረግ እንጀምር? ...... 11

3.3 የጸሎት ቤት እንዴት እናዘጋጅ? ...... 12

3.4 የጸሎት ቤት እንዴት ይሰናዳል? ...... 12

3.5 ስዕለ አድኖዎችን በተመለከተ ...... 12

3.6 ስዕለ አድኖዎችን እንዴት እንደርድር? ...... 13

3.7 ስዕለ አድኖዎችን ከደረደርን በኋላ ምን ምን እናሟላ? ...... 13

ክፍል አራት

ጸሎት ...... 14

4.1 የጸሎት መርሃ ግብርና ሰዓታት ...... 14

4.2 ጸሎት ...... 14

4.3 ጸሎት እንዴት እናደርጋለን? ...... 14

4.4 የጸሎት መርሃ ግብርና ሰዓታት ...... 15

4.5 የጸሎት ሰዓታት ...... 15

4.6 ሰባቱ የጸሎት ሰዓታትና የሚጸለዩበት ምክንያቶች ...... 16

4.7 በሥራና በአስገዳጅ ሁኔታ የተወጠረን ሰዎች ምን እናድርግ? ...... 17

4.8 በቃል መያዝ ያለባቸው መዝሙረ ዳዊት ጸሎታት ...... 17

4.9 ቃል የሚያዙ መዝሙራት ...... 18

4.10 ምግብ ስንበላ ምን ብለን እንጸልይ? ...... 19

ክፍል አምስት

አምላክ ስግደት ...... 20

5.1 የተረሳው ትልቁ እና ኃይለኛው ስግደት ...... 20

5.2 እጅግ የዘነጋነው ይህ ስግደት ...... 20

5.3 የአምልኮት ስግደት ለምን ይሰገዳል ...... 21

5.4 የአምልኮት ስግደት መቼ መቼ ይሰገዳል? ...... 22

5.5 የአምልኮት ስግደት እንዴት ይሰገዳል? ...... 22

5.6 የአምልኮት ስግደት ምን ምን እያልን እንስገድ? ...... 23

ክፍል ስድስት

የንስሐ ስግደት ...... 24

6.1 በደላችንን የምናጥብበት ስግደት ...... 24

6.2 የንስሐ ስግደት ለምን ይሰገዳል? 24
6.3 የንስሐ ስግደት መቼ መቼ ይሰገዳል? 25
6.4 የንስሐ ስግድት ምን ምን እያልን እንስገድ? 25

ክፍል ሰባት

የቅዱሳን ስግደት 27
7.1) ኃያሉ የጸጋ ስግደት 27
7.2) የጸጋ ስግደት 27
7.3) የጸጋ ስግደት ለምን ይሰገዳል 27
7.4) የጸጋ ስግደት መቼ መቼ እንስገድ? 28
7.5) የጸጋን ስግደት ምን ምን እያልን እንስገድ? 28

ክፍል ስምንት

የቅዱሳን ስግደት 30
8.1) የክብር ስግደት 30
8.2) የክብር ስግደት ለምን ይሰገዳል 30
8.3) የክብር ስግደት መቼ መቼ የእንሰግዳለን? 30

ክፍል ዘጠኝ

መቁጠሪያ 30
9.1 መቁጠሪያን እንዴት እንጠቀምበት? 31
9.2 መቁጠሪያን ለመጠቀም 32
9.3 በመቁጠሪያ ምን ምን እያልን እንቀጥቅጥ? 33

ክፍል አስር

የጸሎት ቤት መርሃ ግብር 34

ክፍል አስራ አንድ

የጸሎት ሰዓታት ውጊያ 36
11.1) ምን እናድርግ 37

ክፍል አስራ ሁለት

አጋንንትን ስለማሰር 38
12.1 አጋንንትን ለማሰር 38

ክፍል አስራ ሦስት

የጸሎት ውኃ እና ቅባዕ ዘይት 39
13.1) ቅባዕ ቅዱስን በዲያቢሎስ ውጊያ ግዜ እንዴት እንጠቀምበት 39

ክፍል አስራ አራት

ቅዱስ ቁርባን 40
14.1) ቅዱስ ቁርባን ለመውሰድ ምን ያስፈልጋል? 40
14.2) ቅዱስ ቁርባንን ለምን እንወስዳለን? 41
14.3) የቅዱስ ቁርባን 7 ጥቅሞች አራት 41

## *መሠረታዊ የአምልኮት ትምህርት*

### *መግቢያ*

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን**

(መዝሙረ ዳዊት ምዕ. 23)

1፤ እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።

2፤ በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።

3፤ ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።

4፤ በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል።

5፤ በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው።

6፤ ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።

በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ፥ ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህም ትምጣ፤ ፍቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤ የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ፤ በደላችንንም ሁሉ ይቅር በለን፤ እኛም የበደሉንን ይቅር እንላለንና፤ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን፤ ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ፤ መንግሥት ያንተ ናትና፤ ኃይልም ክብርም ለዘላለሙ፤ አሜን።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ፥ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፤ ሰላም እልሻለሁ፤ በሐሳብሽ ድንግል ነሽ፤ በሥጋሽም ድንግል ነሽ፤ የአሸናፊ እግዚአብሔር እናት ሆይ፥ ሰላምታ ላንቺ ይገባል፤ ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ፤ የማኅጸንሽም ፍሬ የተባረከ ነው፤ ጸጋን የመላሽ ቅድስት ሆይ፥ ደስ ይበልሽ፤ ልዑል እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና፤ ከተወደደው ልጅሽ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድም ይቅርታንና ምሕረትን ትለሚኝልን ዘንድ፤ ኃጢአታችንንም ያስተሰርይልን ዘንድ፤ አሜን።

**ይህ << *በማለዳ ንቁ!* >> የሚለው ተከታታይ የትምህርት ዝግጅት በተቀዳሚ ዓላማና የተደራሽነት ራእይ የሚጠቁመው፤ እንዴት በቤት ውስጥ አምልኮት ጠላትን መቋቋምና ማሸነፍ እንደሚቻል፤ ጌታችን ልዑል እግዚአብሔር በሰጠን ጸጋም በመታገዝ የቃልኪዳኑን ኃይልና የተስፋውን እውነት በመግለጥ፤ የበረከቱንና የጥበቃውን የፍቅር አምባ ላይ በመቆም፤ ሁለንተናዊ ምግባረ ክርስትና በዕለት ተዕለት አቋም ውስጥ በመያዝ፤ የመንግሥቱ ወራሾች የምንሆንበትን የሃይማኖት ጉዞ መሠረታዊ መንፈሳዊ መረጃን ነው።**

*<< ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል >>* **ወደ ቲቶ.** 2፥12-13

**<u>አስተውሉ!</u>**

**የሚለቀቀው ሁሉ የጽሑፍና የምስል መረጃ እንጂ ምግባር አይደለም። የተግባሩ ድርሻ የእናንተና የእናንተው ነው። እዚህ ላይ የሚቀርቡት አካሄዶችና ተግባሮች ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ሕይወታችን አኗኗር ካደረስነው የሚወራ ብቻ ሳይሆን የሚታይ፣ የሚሰማ ብቻ ሳይሆን የሚገለጥ፣ የሚጻፍ ብቻ ሳይሆን የሚጨበጥ መንፈሳዊ በጎ ለውጥ አምጥተን በቅዱስ ሥጋና ደሙ በመታተም ለመንግሥተ ሰማያት የበቃን የምንሆንበት ሰማያዊ ጉዳይ ነው።**

ስኳር ካልተቀመሰ እንደሚጣፍጥ ይታወቃል? እሳት ካልተነካ እንደሚያቃጥል ይለያል?

**እንግዲያው በዚህም በማለዳ ንቁ ርዕስ ስር የሚተላለፍላችሁን ትምህርት በምግባር ካላወረዳችሁት ትርጉሙ መቼም አይገባችሁም። ጥቅሙን አትረዱትም። የመስገድ ጥቅም የሚገባችሁ ስትሰግዱ ብቻ ነው። የመጸለይ ኃይል የሚታወቃችሁ ስትጸልዩ ብቻ ነው።**

የመቁጠሪያን ጥቅም የሚያውቀው የተጠቀመበት ብቻ ነው። የቅዱስ ቁርባንን ረድኤት የሚረዳው ገብቶት የሚቀርበው ብቻ ነው። ስለ ጸሎት ቤት የሚገነዘበው ጸሎት ቤት ያለው ነው። የዚህ ጽሑፍ ድርሻ መምሪያ የሚሆንን ትምህርት መስጠት ነው።

ስለዚህ ግዴየላችሁም በምግባር ሕይወታችሁን ቀጥ አድርጉና አቁሙት። ዛሬ ነገ ሳትሉ ባላችሁት እና በሆነላችሁ ልክ የምግባርን እንቅስቃሴ ጀምሩ። በዚህ ንባብ ውስጥ ያሉት "መሠረታዊ የአምልኮት ትምህርቶች" ከምታስቡት በላይ ሕይወታችሁን የሚቀይሩ የሃይማኖት አቅጣጫዎች ናቸው። ካልሞከራችሁት ምንባብ ብቻ ነው የሚሆነው። ስትተገብሩት ግን ሕይወት ይሆናል።

የሰው ልጅ ከእንስሳት የሚለዩት ስለሚያስቡ ነው ትላለች ዓለም። ሐሰት ነው። እንስሳት በራሳቸው ዓለም ስላለማሰባቸው ማን አረጋገጠ? በእነርሱ ልክ በበቂ ደረጃ ላለማሰባቸው እንዴት እናውቃለን? የእነርሱን ዓለም የመግባቢያ አሳብን የት አውቅነው? ይልቅስ እኛ ከእንስሳት የምንለየው እግዚአብሔርን ስለምናመሰግን እና ክብሩን ስለምንወርስ ነው። የተፈጠረንበትንም ዓላማ ይኸው ነው። በጎደለው የዲያብሎስ ነገድ ፋንታ እኛ ክብሩን ለመውረስ ነው የተፈጠርነው። ለዛ ነው ዲያቢሎስ ድምፁን አጥፍቶ በጣም እያጠፋን ያለው። በእርሱ ቦታ መግባታችን በጣም ያስቀናዋል። ይኼ የተፈጠርንበት የሰማያዊነት ዓላማ ከሕይወታችን ሲወጣ ያው በቃ እንስሳቱን እንሆናለን። መብላት፣ መጠጣት፣ ቤተሰብ መመሥረት፣ መውለድ እና መሞትን እንስሳትም ያደረጉታል። እነዚህን ተፈጥሮዋዊ ዑደቶች በተሻለ መንገድ ለማድረግ ስንል መማራችን ብቻውን ሰው አያሰኘንም። አባቶቻችን ሳይማሩ ከኛ በላይ ሰው ሆነው ክብራቸውን በዓለም አስነብበዋል። መልካም ኑሮ ለመኖር ሌት ተቀን ለገንዘብ ብቻውን መልፋት ሰው አያሰኘንም። አዋፋትም ቀንጆ ጎጆ ለመገንባት ውጣ ውረድን ያሳልፋሉ። ስለዚህ ሰው የመሆኛው ቁልፍ ምንድነው? ሰው የመሆኛው ቁልፍ ሰው ሆኖ መጥቶ፤ በስውር የሚወጋንን ጠላት እንድናሸንፈው አርአያነቱን ገልጦ፤ ሥጋና ደሙን ትቶ፤ የሰውነትን አኗኗር ያሳየንን አምላክ አካሄድን እና መመሪያዎችን ተቀብሎ ሰው ሆኖ መኖር ነው። ባሳየው አቅጣጫ ላይ መመላለስ ነው የሰውነት ቁልፉ።

ዓለም ውሸታም ስለሆነች እናንተም ውሸታም አትሁኑ። ዓለም ዝሙትን አብረቅርቃ ስለምታስተምር በመሰሴን ኃጢአት አትውደቁ። ዓለም ኑሮዋን ለማቅለል ቴክሎኖጂ ውስጥ ስለተጠቀለለች በዛ ውስጥ ገብታችሁ እልም ብላችሁ አትጥፉ። ዓለም የኑሮ ከፍታ መለኪያው ሃብት ነው ስላለች ሃብታም ለመሆን ብቻ አትሯሯጡ። ዓለም ስለ ዘላለም ሕይወት አትነጨቅላችሁም። ይልቅ ዓለም ውስጥ ዲያቢሎስ ብዙ ነገርን ይዞ ከብቦ ከውሰጥም ከውጪም ያጠቃናል።

ስለዚህ ዓለም ውስጥ ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ነው ኃያሉ ነገር። እግዚአብሔርን ሳታውቁት እንዳትሞቱ። የአምልኮት ስግደትን ብርሃን ሳትረዱ ግዜ እንዳይቀድማችሁ። ጠላት ላይ ሳትነቁ እንዳታልፉ። ለሌላው በረከት የመሆንን አቅም ሳታገኙት እንዳታልፉ።

በዚህ ጽሑፍ የሚሰጡትም ሆነ እንደ ግል የማስተምራቸው መረጃዎችና ትምህርቶች በሙሉ በእውነተኛ አምልኮ ውስጥ የተገኙ ሙሉ በሙሉ መንፈሳዊ የሆኑ ተጨባጭ ናቸው።

ማንኛውም ግለሰብ መረጃዎቹንና ትምህርቶቹን ወደ ምግባር በመቀየር ተጨባጭነቱን በሕይወቱ ማረጋገጥ ይችላል።

የሚሰጡት መረጃዎችና ትምህርቶች መሠረታዊ ውጤት የሚከተሉት ናቸው።

1. የአምልኮት ስግደትን ትልቅ መፍትሔነት መገንዘብና ክርስትናን በምግባር ማነጽ

2. ሰውነትና ሕይወት ውስጥ የተደበቁ ርኩሳን ጠላቶችን መለየትና በግብራቸው ላይ ነቅቶ መልሶ መውጋት

3. ለእውነትና ለበረከት የሚሆን አኗኗርን በኑሮ ውስጥ መያዝና መግለጥ

4. በዙሪያ ያሉ ቤተሰቦችንና ወዳጆችን ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ሕይወት በማምጣት የክርስቶስን በረት በጠፉ በጎች የመሙላትን ጉዞ ማወቅና መተግበር

እንግዲህ የአምልኮት ትምህርቱ ርዕስ፤ 'በማለዳ ንቁ ' የሚል ነው። በማለዳ - ንቁ!

ዛሬ በተገኘንበት የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ያለን ኢትዮጵያውያን ትውልዶች በሃይማኖታዊ እውነትና ታሪክ ውስጥ የቆየትን ቀደምት አባቶችና እናቶቻችንን ተጋድሎ እንደ ኋላ ቀርነት ቆጥረን፤ ተጉዘው የመጡበትን የቃልኪዳንና የጸጋን ጎዳና ንቀንና አዋርደን ስለናድነው፤ በቀደመው የአባቶቻችን ዘመን ተሸንፎ የነበረው ሠራዊት በቁጭትና በእልህ አንሰራርቶ ቂሙን ሊወጣብን በግፊትና በፍጥነት ዘምቶብን፤ ከቤተእግዚአብሔር እስከ ዓለማውያን ቦታዎችና የዘመን ገጽታዎች ድረስ ሰፋፊ ውድመቶችንና የትውልድ ቁስለቶችን አድርሶብን፤ ያለፈ ታሪክ ብቻ ባለቤት ሲያደርገን አልነቃንበትም። ቅዱስ ጳውሎስ << ንቁ >> ባለገራችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና ያለው ይህንን የታሪክ ጉዳቶችንና የርኩሳን መናፍስት በሚስጢራዊ ወጥመድ የተወሳሰበን ከፍተኛ የዘመን ኪሳራን ለማስገንዘብ ትውልዱን ሲያሳስብ ነበረ። እኛ ታዲያ መቼ ነው የምንነቃው ?

የማመዛዘን አቅማችንና የሕሊናችን የማስተዋል ክፍል ተሰልቦ ንቁ የሚለው ጉዳይ ላይ በልቦና እና በማጤን ላይ የማስተዋል ቀልብ አቅምና ጉልበት ስላጣን ወደ ምድር የተጣሉት ጠላቶቻችን ተጫወቱብን። በጣም ተጫወቱብን። ከየግለሰቡ ኑሮና ጓዳና ጀምሮ በትላልቅ የአገር አጀንዳዎችና መሠረታዊ የማሕበረሰብ ግንባታዎች ላይ ሳይቀር ሥር የሰደደ ችግሮችና ጥፋቶች ሲከናወኑ ልንነቃ የሚያስፈልግበት የሕይወት ደውል ይሆነን ነበረ። ግን አዚም ሆኖ የያዘን ጠላት ጆሮዋችንንም ልቦናችንንም ስላደበዘዘው መንቃት አቅቶን ፍዝዝ ድንግዝ ባለ አኗኗር መካከል ጠፍተን ግራ ተጋብተን፤ መንፈሳዊ ኃይልና ሞገስ የተለየው ጉዟችንን ስንመለከት የክፉት ሠራዊቶች ወጥነው የተነሱብትን ያለፈ ቂም የመወጣት ሴራቸውን በሰፊ አድማስና በጥልቀት እንዳስፈጸሙ ልንክደው የማንችለው ሃቅ ሆኖ ይታያል። አሁን በእርግጠኝነት እያንዳንዳችን በአምልኮተ እግዚአብሔር ሕይወት ዕለት በዕለት መገኘት ስንጀምር፤ በሕይወታችን ውስጥ ከእውቅናችን እና ከመረጃ ርቀታችን ውጪ ባላጋራ ጠላት ሆነው የተሸሸጉት ክፉ መናፍስት መገለጥ ይጀምራሉ።

"በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ፥ በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ፥ እጠብቃለሁም።"

(መዝሙረ ዳዊት 5፥3)

በአንድ ወቅት ቅዱስ ዳዊት በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ፥ በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ፥ እጠብቃለሁም አለ። በማለዳ ሲል አንድም በጠዋቱ ክፍለ ጊዜ ለአምልኮትና ለምስጋና እገኛለሁ ሲል፤ በሌላም ደግሞ በማለዳ ሲል ጊዜው ሳይረፍድ፣ ጠላት ሳይቀድም፣ በቶሎ ለእግዚአብሔር ኖርሁ እንደማለትም ነው።

"ንቁ፥ በሃይማኖት ቁሙ፥ ጎልምሱ ጠንክሩ። በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን።"

(1ኛ. ቆሮን ምዕ. 16፥13)

ስለዚህ በማለዳ ንቁ ሰንል፤ በማለዳ ድምፃችንን እያሰማን በጊዜ ሳይረፍድብን ነቅተን በሃይማኖት እንቁም፣ እንጎልምስ፤ ጠንክረንም በእምነት ድጋፍ በኩል ርኩሳን መናፍስትን እያሸነፍን በምድርም በሰማይም ዋጋ ያለው ሕይወት እንኑር ለማለት ነው።

<u>ከመምህር ግርማ ተማሪ ናትናኤል</u>

## ክፍል - 1

## <u>የእግዚአብሔር ፍቅር</u>

ከሁሉ አስቀድሞ እውነተኛ ክርስቲያን ለመሆንና በእግዚአብሔር ጥላ ስር ዘመንን ለማሳረፍ ብሎም ክፉ መናፍስታችን ለማስቀም በመጀመሪያ ምን ከማድረግ እንጀምር?

የመጀመሪያው ትልቁ የእምነት መነሻና የሃይማኖት ግምባታዎች እና የጉዞ አካሄዶች ሁሉ መሠረት እና መድረሻውም ጭምር ከአምላክ ጋር በፍቅር መጨባበጥ ነው!!

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።

“ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።” ዮሐንስ 4፥8

ፍቅር በራሱ እግዚአብሔር ነው። በቤተክርስቲያናችንም የቅዳሴው ቃል፥ አብ ፍቅር ነው፤ ወልድም ፍቅር ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ፍቅር ነው በማለት የሰማዩ አባት ፍቅር እንደሆነ ይናገራል። እንደ ክርስቲያን ከመጀመሪያ ይህን ማወቅና ማመን ያስፈልጋል። በቃ ቃሉ እንደዚህ ነው የሚለው 'እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።'

የትኛውም እውነተኛ ፍቅር ከእግዚአብሔር ይጀምራል። በእግዚአብሔርም ይመራል። ከእግዚአብሔር ጋርም ይቀጥላል። የፍቅር መነሻም መድረሻም ልዑል እግዚአብሔር ብቻ ነው። የፍቅርን አባት፣ የሰላም አለቃ መድኃኒዓለም በራሱ ፍቅርነት እኛን ሲወደን ልክም አላበጀለትም። ወሰን በሌለው፣ ድንበር ባልያዘ ፍጹም ፍቅር እርሱ አፈቀረን።

" በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።"

(ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥37)

እርሱ አዶናይ ዓለምን ሁሉ በቃሉ ፈጥሮ ሳለ ዓለምን ጠቀለለና በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በኩል እግዚአብሔር ቃል በሥጋ ተዛመደን። በሥጋ እስኪ.ወለድም፤ ከእኛም እንደ አንዱ ይሆን ዘንድ በጥልቅ ወደደን። ወደደን እናም አምላክ ሲሆን የሰው ልጅ ሆነና ከኛ ወገን ሆነ። አማኑኤል ሆነ።

" እግዚአብሔር አምላክም አለ። እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤ "

(ኦሪት ዘፍጥረት 3፥22)

ተመልከቱ! ቃሉ እንዲህ ነው የሚለው።

"እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል።” ዮሐንስ 4፥11

እግዚአብሔርን እንዲህ አድርጎ ከወደደን ይላል። በአባቱ አምላክ ነው። በእናቱ ወገናችን። ወገናችን እስኪሆን ድረስ ሰውን ወደደ ማለት ነው። ከዛ ደሞ እኛም ልንዋደድ ይገባናል ይላል። እግዚአብሔር በራሱ ፍቅር ነው። በእርሱ ፍቅር ደሞ እኛ በፍቅር እንኖራለን። በሰጠንም የሕያውነት እስትንፋሱ ውስጥ ማኅተብ ሆና በተቀመጠች ፍቅሩ ሁሉንም እናፈቅራለን። ምንም አይነት ፍቅር ከእግዚአብሔር ፍቅር ካልጀመረ መድረሻ አይኖረውም። መድረሻ ቢኖረውም ፍፃሜው አያምርም።

እነሆም ታዲያ

የእምነት ኃይል ከእግዚአብሔር ፍቅር ካልተነሣ ዋጋ የለውም። እግዚአብሔርን ማፍቀር ለሁሉም መሠረቱና መነሻ ነው። ታላቂቱና መነሻይቱም የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው።

ሰማያዊ ቃሉ እንደዚህ ይነበባል።

"ኢየሱስም እንዲህ አለው። ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም። ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት።" የማቴዎስ ወንጌል 22፥37-40

ነፍሱን የሰጠንን መድኃኔዓለምን ከእውነትና ከልብ እናፍቅረው። ስንሰገድ በፍቅሩ ይሁን! ስንጸልይ በፍቅሩ ይሁን! ስንጾም በፍቅሩ ይሁን!

ዲያቢሎስን ሸሽተን ሳይሆን መድኃኔዓለምን ሽተን ነው ፍቅርን መስጠት ያለብን!

ጸሎት፣ ስግደትና ጾም ስራ የሚሆንብን

አንደኛ• ለእግዚአብሔር የምንከፍለው ውለታ እንደሆነ አድርገን ስንቀበል

ሁለተኛ• ከእግዚአብሔር የሆነ መሻታችንን ለመሙላት ብቻ ስንጠቀምባቸው

ሦስተኛ• አጋንንትን ለማሳደድ ብቻ ስንጠቀምበት ነው።

አምላክን በቀጥታ አፍቅረን ሲሆን ግን ለፍቅሩ እንሰግዳለን። ለፍቅሩ ነው የምንበረከከው። ለፍቅሩ እንጸልያለን። ይኸውላችሁ 'ከልብ ጸልዩ' የሚባለው እግዚአብሔርን አፍቅራችሁ ተመላለሱ ለማለት ነው። ሰይጣንም አጥብቆ የሚጠላውና የሚያሸንፈው የፍቅር አምልኮት ነው።

እስኪ እንፈትሽ። እግዚአብሔርን እውን አፍቅረናል? ሕይወታችን ውስጥ ፍቅሩ አለ ወይ? ስንሰግድ ፍቅሩ አለ? ስንጾምና ስንጸልይ ወደን ነው? የእውነት እግዚአብሔርን እንወደዋለን? ወደ ውስጥ ወደ ልባችን እንፈትሽ።

ከሁሉ አስቀድመን ለፍቅር እንመላለስ። ፍቅርን ሳትይዙ አንድ ስንዝር አትጓዙም። ብትጓዙም እንኳ ዋጋ የላችሁም።

" የጐመን ወጥ በፍቅር መብላት የሰባ ፍሪዳን ጥል ባለበት ዘንድ ከመብላት ይሻላል። "(መጽሐፈ ምሳሌ 15፥17)

ፍቅር የሌለው እምነትና ጠባይ ውስጥ ክፋት ይደበቃል። ግራ ዘመምነት ተሰውሮ በኑሮአችን ውስጥ ኑሮ ሆኖ፤ እውነታ ያጣ ከላዩ ብቻ የነጣ፤ ከውስጡ ግን የጠቀረን የአኗኗር ገጽታን እንድንላበስ ይሆናል። በዘመናችንም ርኩሳን መናፍስት ወደ ቤተ እግዚአብሔር በመቅረብና በዚያም ውስጥ በመመሸግ መንፈሳዊውን ጉዞና ሕይወት ልምምድ ለመዳፈር የጀመሩት በዚህ ፍቅር ከሌለበት ሕይወታችን ውስጥ ስፍራና ቦታ ስላገኙ ነው።

ግን ይኸውላችሁ ቅዱስ ቃሉ እንዲህ ይላል።

ወደ ኤፌሶን ሰዎች 5፥1

"እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፥ ክርስቶስ ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ።"

የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ንጹሕ ፍቅር ለማወቅና በውስጡም ለመኖር አስቀድማችሁ አስቡ። መድኃኔዓለምን አጠገባችሁ እንዳለ አባት ከማፍቀር ሁሉን ጀምሩ። ከዚህ ካልተነሣችሁ መድረሻ የላችሁም። ፍቅር ከሁሉ ይበልጣል። ፍቅር ከሁሉ ይቀድማል። ስለዚህ መመሪያ አንድ፤ ትምህርት አንድ ስንል የእግዚአብሔር ፍቅር ብለን እንጀምራለን።

(1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ምዕ. 13)

----------

1፤ በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ።

2፤ ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።

3፤ ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።

4፤ ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤

5፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤

6፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤

7፤ ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።

8፤ ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል።

9፤ ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤

10፤ ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል።

11፤ ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር፥ እንደ ልጅም አስብ ነበር፥ እንደ ልጅም እቈጥር ነበር፤ ጎልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ።

12፤ ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ።

13፤ እንዲህም ከሆነ፥ እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።

## ክፍል - 2

### ክርስቶስን በመከተል በሃይማኖት መገለጥ

<< የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ>> ኤፌሶን 6፥10-18

በእውነተኛ ክርስትና ውስጥ ዘመንን ለማሳለፍ፣ በአፍ ሳይሆን በምግባር የተገለጠ ሰማያዊ አኗኗርን ለመገንባትና ርኩሳንን መናፍስትን በእግዚአብሔር ክንድ ጥሎ በጸጋውና በኃይለ መለኮቱ በኩል ለመሰለፍ የመጀመሪያው እርምጃችን መድኃዓለምን ከልብ ማፍቀር ነው ብለናል።

" *የጥበብ_መጀመሪያ* እግዚአብሔርን መፍራት ነው፥ ለሚያደርጓትም ሁሉ ደኅና ማስተዋል አላቸው፤ ምስጋናውም ለዘላለም ይኖራል። " (መዝሙረ ዳዊት 111፥10)

እግዚአብሔርን የምንፈራው አስቀድሞ ስናፈቅረው ነው። ምንም ነገር ከእግዚአብሔር ፍቅር ካልተነሳ ባዶ ነው። ከንቱ ነው። እምነት ውስጥ እግዚአብሔርን ማፍቀር ከሌለ ዋጋ የለውም። እግዚአብሔርን ማፍቀር ለሁሉም መሠረቱ ነው።

"ኢየሱስም እንዲህ አለው። ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም። ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት።" የማቴዎስ ወንጌል 22፥37-40

ክርስትናችንን ከእግዚአብሔር ፍቅር ካስጀመርን በኋላ አስከትለን ምን እናድርግ? ይህንን የሚመልስልን የመጽሐፍ ቅዱስ ምሪት እንመልከት።

"በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ። የዲያቢሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ከስልጣናት ጋር ከዚህ ጨለማ ዓለም ገዥዎች ጋር በሰማይ ስፍራ ከነበራቸው ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ በክፉ ቀን ለመቃወም፣ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፣ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፣ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፣ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉዎች ፍላፃዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነት ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ። "

ቃል በቃል ብታነቡት እያንዳንዱ ቃላት ላይ በአምልኮት ሕይወት ውስጥ እንዴት ነው የርኩሳን መናፍስትን ጥቃትና ስውር ወጥመዶች መቋቋም የሚቻለው የሚለውን ጥያቄ የእውነቱን መልስ መጽሐፍ ቅዱስ አስቀምጦታል። "የዲያቢሎስን ሽንገላ እንድትቃወሙ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ልበሱ" ይላል አንደኛው ክፍል። በሌላኛው ክፍል "የእምነት ጋሻ አንሡ" ይላል።

### 2.1) የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ የሚባሉት ምንድን ናቸው?

ማርቆስ 12፥17 <<ኢየሱስም፣ “የቄሣርን ለቄሣር፥ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ” አላቸው። እነርሱም በእርሱ ተደነቁ።>>

የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ የሚባለው ከእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ ነው። ከእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ ደሞ እውነተኛ በሕይወት የተጨበጠና ለሌላው መድረስ የሚችልን የክርስትና መገለጥን የያዘው ሁሉ ነው። ይህንን የክርስትና መንገድ ደግሞ በሰማያዊ ኃይልና ሞገስ ጠብቃ፣ በእውነተኛ የታሪክ መሠረትና የቃልኪዳን ምሪት ገንብታ፣ በአምላክም ጸጋና የረድኤት ሥልጣን ታግዛ፣ በቅዱሳንም የጽድቅ መንፈስ ምሳሌነት ተመርታ፣ በመሰዋትነትና በጽናትም ጽንታ የቀመች ደግሞ አንድ የእውነት ሃይማኖት ብቻና ብቻ ናት።

(ወደ ኤፌሶን ሰዎች ምዕ. 4)

5፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤

6፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።

አንዷቷ ሃይማኖት ናት የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ እውነተኛ መጋዘን።

<< እግዚአብሔር እንዲህ ይላል "በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውን መንገድ ጠይቁ፤ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ፤ በእርስዋም ላይ ሂዱ፤ ለነፍሳችሁ እረፍት ታገኛላችሁ። እነርሱ ግን አንሄድባትም አሉ።" ትንቢተ ኤርምያስ ምዕ 6፥16 >>

የቀደመቺው መንገድ አንዷቷ ሃይማኖት ናት። መልካሚቱ መንገድ ሃይማኖት ናት። ለነፍስ እረፍት የምናገኝባት ማረፊያ ሃይማኖት ናት።

ይህንንም ሐዋሪያው በቆሮንቶስ መልእክቱ ላይ ተናግሮታል።

<< ንቁ በሃይማኖት ቁሙ ጎልምሱ ጠንክሩ በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን።>> 1ኛ ቆሮ.16፥13

በሃይማኖት ቁሙ አለ። አስቀድሞ ኤርሚያስ የቀደመቺውን መንገድ ጠይቁ፤ በእርስዋም ሂዱ ብሏል። ሐዋሪያው ቁሙ ሲለን፥ ነብዩ ሂዱ ሲለን ሃይማኖትና መልካሚቱ መንገድ በአንድ ትርጉማ ውስጥ የተሰጡን የእምነት የጎዳና አቅጣጫዎች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልገናል። ሃይማኖት መንገድ ስለመሆኗ ክርስቶስ በሰማያዊ ቃሉ እንደዚህ አለ።

" ኢየሱስም። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" (የዮሐንስ ወንጌል 14፥6)

ጌታችን እኔ መንገድ ነኝ በማለት፤ በስሙ ክርስቲያን አሰኝቶን ወደ መንግሥቱ እንደሚወስደን ነገረን። ክርስቲያን ከሆነ ውጪ፤ ወደ አብ የሚመጣ የለም አለ። እውነተኛውን መንገድ መከተል ክርስቶስን በመከተል ክርስቲያን ያሰብላልና።

ስለዚህ ትምህርት አንድ ብለን ክርስቶስን ማፍቀር ብለን ተምረናል። ትምህርት ሁለት ክርስቶስን መከተል ይሆናል ማለት ነው። እግዚአብሔርን ከማፍቀር ለምን እንደተነሣን ገባችሁ? እንከተለው ዘንድ ነው። ሳታፍቀረው ዝም ብለህ ብትከተለው፤ ሌሎች ሲከተሉ አይተህ ወይ በቃ እንደው ለዘልማድ ብቻ ነው የሚሆነው። ስታፈቅረው ግን በርሱ በመንገዱ ስትሄድ ታምነዋለህ። በጉዞህ ላይ ብትሰነካከል ያነሣህ ዘንድ ትጠራዋለህ። ጉዞው መከራና ስቃይ ቢያገኘው ስለወደድከው ስለ እርሱ ብለህ ትጸናለህ። ከፊት እየቀደመ እንደሚመራህ፤ ከኋላ እየተከተለ እንደሚደግፍህ ታውቅማለህ።

### 2.2) በሃይማኖት መቆም፥ በእውነተኛዋ መንገድ መሄድ ምን ማለት ነው?

በቀጥተኛ ገለጻና አነጋገር በሃይማኖት መቆም ማለት ዘወትር በመንፈሳዊ ምግባርና በእምነት ሕይወት በተግባር መመላለስ ማለት ነው።

### 2.3) መንፈሳዊ ምግባርና ሕይወት ምን ምን ከማድረግ ይነሣል?

1ኛ• በቤት ውስጥ የጸሎት ቦታ፣ ስፍራና ጊዜ ማበጀት

2ኛ• የዘወትር የአምልኮት ስግደትና ምስጋና

3ኛ• ሰባቱ የዘወተር ጸሎተ ግዜያት ላይ መንበርከክ

4ኛ• በጾም መገኘት

5ኛ• ዐሥራት በኩራት ማውጣት

6ኛ• ንስሐ መቀበል

7ኛ• ቅዱስ ቁርባን መውሰድ

8ኛ• የእግዚአብሔርን ቃል ዘወትር መከተል

9ኛ• ከክፋት መሸሽና መቃወም

10ኛ• በበረከቱ ጎዳና በኩል ለመሰለፍ መጣር

(ወደ ኤፌሶን ሰዎች ምዕ. 4)

----------

1፤ እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ፤

2፤ በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም፤ እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ፤

3፤ በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።

4፤ በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤

5፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤

6፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።

7፤ ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን።

## ክፍል - 3

## የጸሎት ቤት

ክርስትና አሳብ አይደለም። ክርስትና እቅድ አይደለም። ክርስትና ልማድ አይደለም። ክርስትና ባህልም አይደለም። ክርስትናን ጊዜ አይገድብም። ነጣላ ሲወልቅ አብሮ የሚወልቅ አይደለም። ክርስትና የዕለት ዕለት ኑሮ ነው። ክርስትና ዘወትር ክርስቶስን መከተል ነው። ቃሉን ተመልከቱ።

" ለሁሉም እንዲህ አላቸው። በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ።" (የሉቃስ ወንጌል 9፥23)

ክርስትና የሁልግዜ ጉዞ ነው። በእያንዳንዱ የሕይወታችን ቅጽበት ልንከተለው የሚገባው መንገድ ነው። ክርስትና ዛሬ ጀምረን ነገ የምንተወው የሰሞን ብልጭታ አይደለም። ዕለት ዕለት ይከተለኝ ነው እኮ የመድኃኒዓለም ሰማያዊ ድምፅ ያለው።

### 3.1) ታዲያ በክርስትና ዕለት ዕለት እንዴት መኖር እንችላለን?

ለዚህ ቀጥተኛውና ግልጹ ምላሽ ዘወትር በምንገኝበት ቦታ ላይ ለአምላካችን አዶናይ እግዚአብሔር ራሳችንን በፍቅር አምልኮት በማስገዛት አካሄዳችንን በመለኮቱ ምሪት ላይ መዘርጋት የሚለው ይሆናል።

### 3.2) ይህንን ለማድረግ ምን ከማድረግ እንጀምር?

" እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ፥ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ፥ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን። "(መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 24፥15)

አብዛኞቻችን በብዛት ሰፊ ጊዜያችንን የምናሳልፈው፣ የምናርፈው፣ ኑሮአችንን የምንመራው፣ ቤተሰብ የምንመሠርተውና ወዘተ... ከቤታችን ሆነን ነው። ስለዚህ ክርስትና ከመሠረታችን ከቤት መገለጥ ይገባዋል። ብዙዎቻችን ክርስትናን የምናውቀው ቤተክርስቲያን ስንገባ ብቻ ነው። ቤተክርስቲያን መቀደሻችን፣ መባረኪያችን፣ ቃለ ወንጌሉን በአንድ ላይ መስሚያችን፣ በጋራ ማመስገኛችን፣ ሥጋና ደሙን መቀበያችን፣ በጽላቱም መባረኪያችን፣ ማስቀደሻችን ናት።

ታዲያ ግን ሁሉም ክርስቲያን ሊባል የጣቶች ቁጥር የቀረው በሚመስል ደረጃ ከቤተክርስቲያን ሲወጣ ክርስትናውም በዛው ይወጣል።

ክርስትና የዕለት ተዕለት ምግባር ከሆነ ግን ዕለት ዕለት ከምንገኝበት ቤት የሚኖር የአምልኮት ግዜና ቦታ ያስፈልገናል።

ምክንያቱም፦

❖ አንደኛ ዘወትር የሰላም ኑሮን እያገኘን እንሄዳለን። ሰላም የሚጀምረው ከውስጠኛ ክፍላችን ነው። እነሆም ዘወትር በቤታችን የጸሎት ቦታና ጊዜ ካለን የሰላም አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቤታችን ይገባልና ሰላማችን ከውስጣችን ወደ ቤታችን፤ ከቤታችን ወደ ዓለም እየበዛ እየበዛ ይሄዳል።

❖ ሁለተኛ ክፉ መናፍስትን በየዕለቱ እየተቃወምን እንከላከላቸዋለን። ይህም ማለት፦

❶• ከውስጥ በኩል ያደፈጠ ጠላት እየተዳከመ ይመጣል።

❷• ቤታችን ውስጥ አስቀድመው የነበሩና ያሉ መናፍስቶች ከቤታችን ለመራቅ ይገደዳሉ።

❸• የቤተሳባችን አባላት ላይ ያደፈጠ ጠላት አምልኮታችን ይበጠብጠዋል። ከበረታንም ይጋለጣል።

❹• ሰፈራችን አቅራቢያ የሚልከሰከሱ እንደ የዛር፣ የመናፍቅ፣ የቡዳና ወዘተ... መናፍስት እይታቸው ይደበዝዛል። ከእኛ መራቅና መሸሽ ይጀምራሉ።

❺• ከስራ ቦታ ከትምህርት ቤት አስቀድመው አልፈው ወጥመድ የሚያዘጋጁ እንደ ዓይነጥላ ያሉ መናፍስት ግብራቸው ይከሽፋል።

❻• በመንገዳችንና በጉዛችን ላይ የሚኖሩ የሰላቢ፣ የቡዳ፣ የቁራኛና የሱሉስ ዝውውር መናፍስት በሙሉ የአምልኮት መለኮታዊ ከለላ ስላለን ሊጠጉን አይቻላቸውም።

❖ ሦስተኛ ራእይና የእግዚአብሔር መልእክትን ለሕይወታችን ምሪት ይሆነን ዘንድ በቃልኪዳኑና በተሰፋው ኃይል በኩል በየግዜው እናገኛለን።

❖ አራተኛ 'የነገን አንተ ታውቃለህ 'ብለን ጸልየንና ሰግደነ መተኛት ስንለምድ፤ የነገውን ለእግዚአብሔር ሰጥተናልና ሳንጨነቅ የምንውልበትን የሕይወት ዕድል ከተከፈቱ መልካም አጋጣሚዎች ጋራ እናገኛለን።

የጸሎት ቤት የግድ ሁሉም ክርስቲያን ሊኖረው ያስፈልጋል። የግድ ነው። ምን ያህል አስፈላጊና ወሳኝ የክርስትና ክፍል እንደሆነ የምትገነዘቡት፤ ከሰራችሁት በኋላ በውስጡ መኖር ስትጀምሩ ነው። የጸሎት ቤት ከሌለህ፡ ወሬኛ፣ ዝም ብሎ ተቀማጭ፣ በሃይማኖቱ ላይ የተኛ፣ ከሚያልፈው ጋር የሚያልፍ፣ ግዜው እንደሆነው የሚሆን፣ የርኩሳን መናፍስትና ክፉዎች ተጠቂ፣ በረከትና ረድኤት ያጣ ኑሮ መሪ፣ ፍቅርና ደስታ የተለየው ሕይወት ገፊ፣ የሰማይ ኃይልና ሞገስ ያጠረው፣ እውነተኛ የእምነት ጉልበትና መገለጥን የማይረዳ፣ ከቤተሰብና ወዳጆች ጋር የማይስማማ

የቁም ሟች ለመሆን ትገደዳለህ። እንኪያስ፡ ጸሎት ቤት መስራት የግድና የግድ ነው።

### 3.3) የጸሎት ቤት እንዴት እናዘጋጅ?

የጸሎት ቤት በመኖሪያ ቤታችን ውስጥ የምንገነባው ትንሽዬ መቅደስ ማለት ነው። መቀደሻችን የሆነ ቦታ ነው። የቤተክርስቲያን መቅደስ ደግሞ ማስቀደሻችን ናት። መቀደስና ማስቀደስ በአንድነት ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መገኘት ይኖርባቸዋል።

የጸሎት ቤት ሲዘጋጅ፡ ከሆነልን ራሱን የቻለ ክፍል ለብቻው መስጠት። የማይሆንልን፡ ባለቺው ክፍት ቦታ መጠቀም። እግዚአብሔርን ባለን ልክ የምናመሰግነው አባት ነው።

### 3.4) የጸሎት ቤት እንዴት ይሰናዳል?

አንደኛ ✓ ቤታችንን በንስሐ አባታችን ወይንም በካህን ሁሉንም ያለውን ክፍል ጸበል ማስረጨትና ማስባረክ።

ምክንያቱም በቤታችን ውስጥ የሚገኙ ርኩሳን መናፍስትን ያሸሻልና። የሚባርክል ካህን ለግዜው ካላገኘን ግን፤ እስከምናገኝ እራሳችን ጸበልን አምጥተን በስሙ ባርከን ለጸሎት ክፍል የመርጥነውን ቦታ መርጨት። መርጨት የማንችል በጨርቅ በመንከር የጸሎት ስዕለ አድንኖዎቹን የምንለጥፍበትን ግድግዳ በስሙ እንዲባርክልን እየጸለይን እንጠርጋለን።

ሁለተኛ ✓ የምሥራቁን አቅጣጫ የተከተለ የግድግዳችን ስፍራ ለጸሎት ቦታ የተመረጠው ነው።

ምክንያቱም በቅዱስ ቃሉ "በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ።" (የዮሐንስ ወንጌል 9፥5) ጌታችን ብሎናል።

ብርሃነቱን በፀሐይ እንወክላለን። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ብሏልና። የፀሐይ መውጫ ደግሞ ምሥራቅ ናት። እመቤታችን አማናዊት ምሥራቅ ናት።

" ኢየሱስም በይሁዳ ቤተ ልሔም በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን በተወለደ ጊዜ፥ እነሆ፥ ሰብአ ሰገል። የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ።" (የማቴዎስ ወንጌል 2:1-2)

ሰብአ ሰገል የክርስቶስን መንገድ ያገኙት የምሥራቁን መንገድ ተከትለው ነው። እኛም እንዲሁ በጸሎት ቤታችን የክርስቶስን መንገድ እንፈልጋለንና ወደ ምሥራቅ ዞረን የፍቅር አምልኮን በቤታችን እንሰዋለን።

ሦስተኛ ✓ በመቀጠል ያሰናዳነው ግድግዳ ላይ

በጥሩ የተሰሩና በጽዳት የተጠበቁ፣ የተባረኩ፣ ቅባዐ ቅዱስ የተቀቡ፣ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሥርአትን የጠበቁ ስዕለ አድኖዎችን በሚገባቸው ሥርአትና ደንብ እንደረድራለን።

ምክንያቱም ስዕለ አድኖዎች እንዲሁ የመገለጫ ስዕሎች የሚሆኑት እንዲሁ ባገኘንበት ለጥፈን ለጌጥና ማድመቂያ ስንጠቀማቸው ነው። አባቶቻችን ግን ስዕለ አድኖዎችን ሲያዘጋጁ ለጸሎት እንዲውሉ፣ ኃይለ መንፈስ ቅዱስ እንዲያርፍባቸውና የተጠቀመባቸውም ሁሉ ከዚሁ በረከት እንዲካፈል በማለት ነው። እኛም ለዚሁ አገልግሎት ስንጠቀማቸው የክርስትናችን ጉልበት ይሆናሉ።

### 3.5) ስዕለ አድኖዎችን በተመለከተ

ከላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔርን ባለን ልክ የምናመሰግነው አባት ነው። ስለዚህ በአቅማችን ልክ ስዕለ አድኖዎቹን መጠቀም የግድ ነው። እንዲሁ ዝም ብለን ስዕል ናቸው ብለን ያገኘውን ስዕል መግዛት አግባብ አይደለም። ከሆነልን፥ በቀንጆ ፍሬም የተዘጋጁ ከቤተክርስቲያን አከባቢ የሚሸጡትን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሥርአትን እና የቅዱሳኑን ክብር በሚገባ የሚገልጡትን መግዛት ነው። ካልሆነልን በሚቻለን ልክ መግዛት። ክርስቶስ የቢሮክራሲ አምላክ አይደለምና ባሚለነው ልክ የሚቀበለን አይደለም።

(ስዕለ አድኖዎችን እንዲሁ ከመንገድ ከምትገዙ ከቤተክርስቲያን ንዋየ ቅዱሳት መደብራት ብትገዙ ልከኛ ምስሎችን ማግኘት ትችላላችሁ።)

ስዕለ አድኖዎቹ ከታች የተገለጸውን አደራደር መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ገዝተን ብቻ ዝም ብሎ ማኖር አይደለም። የራሳቸው የሆነ የአደራደር ሥርአትና ደንብ አላቸው።

### 3.6) ስዕለ አድኖዎችን እንዴት እንደርድር?

በመቆም ልክ በግንባር ትይዩ ፦ የአጋእዝተ ዓለም ሥላሴን። በዛው መስመር በግራ የመድኃኒዓለምን፤ በስተቀኝ ስቅለቱን፡

ምክንያት የአብርሃሙ ሦስቱ ሥላሴዎች ስዕልን ካስተዋላችሁ ዓለምን የያዙ አባቶችን ያሳያል። አጋእዝተ ዓለም ሥላሴም ስንል ከሁሉ በላይ ያሉ፤ ዓለምን የፈጠሩና ዓለምንም የሚገዙ መሆናቸውን ስናመለክት ከፍ አድርገን በመቆም ግንባር ልክ እንሰቅላለን።

መድኃኒዓለምም ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ ወልድ እግዚአብሔር ነውና በምድር የተመላለሰበትን ወቅት የሚያሳዩ ምስሎቹ ከፍ ተደርገው በጎን በጎኑ ይሰቀላሉ። ስቅለቱን የሚያሳዩ ስዕላት ከሥላሴ ምስል በስተቀኝ ይሆናሉ።

በመንበርከክ ልክ ከግንባር ትይዩ፦ የእመቤታችን ከተወደደው ልጇ ጋር። በግራ የቅዱስ ሚካኤል። በቀኝ የቅዱስ ገብርኤል።

ምክንያት ከሰማይ ተለይቶ በሚሰጥረ ሥጋዌ ምድራዊነትን የተካፈለባት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ከሥላሴዎች በታች ከፍጡራን ግን በላይ ናትና ይሄንኑ እናሳያለን። ግራና ቀኝ ሁለቱ ኃያል ሊቃነ መልአክት ከእመቤታችን አይለዩምና ይህንኑ እናሳያለን።

ከበታች፦ የቅዱሳንን ሁሉ ስዕል በየዘርፋቸው እናደርጋለን።

ምክንያት “ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፥ ለባሪያዬም ለዳዊት ማልሁ።" (መዝሙረ ዳዊት 8፥9) እንዲል ልዑል እግዚአብሔር፤ ከመረጣቸው ቅዱሳን የቃልኪዳን ጸጋና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንካፈል ዘንድ ስዕላቸውን መጠቀም የሕይወት በረከትና መንፈሳዊ አጋር የማግኛ የክርስቲያን ትልቅ ስጦታ ነው።

### 3.7) ስዕለ አድኖዎችን ከደረደርን በኋላ ምን ምን እናሟላ?

ስዕለ አድኖዎቹን በእንዲህ መልክ ከደረደርን በኃላ የሚያስፈልጉንን የጸሎት ቤት ንብረቶች እናዘጋጃለን።

*እነርሱም በዋናነት፦*

- መስገጃ ምንጣፍ
- ምንጣፉ ላይ የሚደረደሩ የጸሎት መጽሐፍት። መቅረት የሌለበት 'መዝገበ ጸሎት እና አርጋኖን' ናቸው። ቢቻለን ሁሉን የጸሎት መጽሐፍት ብንጠቀም ጥሩ ነው። ግን የምንችለው ያህል ቅዱሳት የጸሎት መጽሐፍ እናዘጋጃለን።
- መቁጠሪያ
- በእቃ የተቀነሰ ጠበል፣ እምነት፣ ቅባዕ ዘይት እና ሌሎችንም
- የመቅደስ እጣንና ማጤሻው፤ ሻማና መቅረዝ

(ሌሎችንም የቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳን ንብረቶች በተጨማሪ ማሟላቱ በሆነልን ልክ እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ነውና፤ በቻልነው ልክ ለጸሎት ቤት የተፈቀዱ ቅዱሳን ንብረቶችን ሁሉ ማሟላት።)

*ማወቅና መገንዘብ ያለባችሁ*

✓ በስተምሥራቅ የቤታችን ክፍል የጸሎት ቦታችንን ማድረግ የማንችል፥ በሆነልን ቦታ ማድረግ።

✓ ስንጸልይ ወደ ስዕለ አድኖቹ የመጽሐፍ መግለጫ ያህል ርቀት ጠጋ ብለን ነው።

ምክንያቱም ከተባረኩትና በጥንቃቄ ከተያዙት ስዕለ አድኖዎች የሚወጣው መንፈሳዊ ኃይል በጸሎትና ስግደት ወቅት ከውስጥ ያደፈጠን ጠላት ያቃጥላልና ነው።

✓ የተባረከው እጣንና ሻማ በየሰንበቱ ክብረ በዓሉ እንጠቀማቸዋለን።

ምክንያቱም " የእግዚአብሔር ስም የጸና ግምብ ነው፤ ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል። " (መጽሐፈ ምሳሌ 18፥10)

ስለዚህ በእግዚአብሔር ስሙ የተባረከው ሁሉ የጸናውና የተባረከው ነውና በስሙ ከመቅደሱ ተባርኮ የመጣው እጣን በጤሰ ጊዜ ክፉ ኃይላት ይቅበዘበዛሉ፤ ይሸሹማል።

✓ ጠበሉም ሆነ የትኛውንም የጸሎት ቤት ክፍል ለሌላ አገልግሎት መጠቀም አይፈቀድም።

ምክንያቱም "እርሱም። እንኪያስ የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ አላቸው።" (የሉቃስ ወንጌል 20፥25)

ታዲያም የተባረኩትና በስሙ የተቀደሱት ንበረቶች ሁሉ የእግዚአብሔር ናቸው ለእግዚአብሔር የሚውል አገልግሎት ብቻ ላይ ይውላሉ። ለሌላ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ውጪ በተጠቀምናቸውና እንዳገኘንም የምንጥላቸው ከሆነ መንፈሳዊ ኃያላቸውን እንጥልባቸዋለን።

# ክፍል - 4

## ጸሎት

### 4.1) የጸሎት መርሃግብርና ሰዓታት ማናቸው?

አስቀድሞ በተለዋወጥነው መረጃ መሠረት የጸሎት ቤታችንን በሚገባ የፍቅርና የክብር ልክ በጥንቃቄ ካዘጋጀን በኋላ የሚቀጥለው ክፍል እንዴት እንጠቀምበት የሚለው ይሆናል።

በዘወትርም የመንፈሳዊ የጸሎት ቤት ምግባራት ውስጥ የአምልኮት ስግደት፣ ጸሎትና መቁጠሪያ ሳይቋረጡ፤ ጸሎት ቤት በገባን ቁጥር የምንተገብራቸው የዕለት ዕለት ልምምዶች ናቸው። በምንም መልኩ ዘወትር አ ይ ቋ ረ ጡ ም!!

### 4.2) ጸሎት

ጸሎት ፍጥረታትና እግዚአብሔር የሚነጋገሩበት ሰማያዊ ቋንቋ ነው። ጸሎት የክርስትና ሕልውና ድምፅ ነው። ጸሎት በሃይማኖት የመገኘት ኃይልና መገለጫ ነው። ጸሎት የእግዚአብሔርን ቀኝ መጨበጫ መዳፍ ነው። ጸሎት ከሌለ መንፈሳዊ ሕይወት የለም። መንፈሳዊ ሕይወት ከሌለ የሥጋዊ ኑሮ ድክረታ፣ የክፉዎች ወጥመድና የሰይጣን አጥር ውስጥ ገብተን ዘመናችንን በስቃይና በእንግልት ጠፍተን ለመጨረስ እንገደዳለን።

### 4.3) ጸሎት እንዴት እናደርጋለን?

ልብ በሉ። ትምህርት አንድ፥ ክፍል አንድ ብለን ስንነሣ ከእግዚአብሔር ፍቅር እንነሣለን። የዚህ ምክንያት ሁሉም መንፈሳዊ ምግባራት በመነሻነት ከእግዚአብሔር ፍቅር መገኘታቸው ግድ ስለሆነ ነው። ከእግዚአብሔር ለመውሰድ አትጸልዩ። አስቀድሙና እግዚአብሔርን በፍቅር ለማመስገን ቁሙ። የእግዚአብሔር ፍቅር የተለየው ጸሎት አምጣ ብቻ ነው የሚለው። እንዲህ አድርግልኝ ብቻ ነው የሚያውቀው። እንዲህ አስተካክል ብቻ ነው የጸሎቱ መነሻና መድረሻ። ጸሎት ግን መነሣት ያለበት ከምስጋና ነው። ከፍቅሩ ነው። "አባት ሆይ እስከዚህች ግዜ እስከ መላ ኃጢአቴ አቀምከኝ፥ እንደምን ትወደኛለህ? እኔም እንዳንተ እወድህ ዘንድ ፍቅርህን አካፍለኝ።

ጠባያቶቼ ከሰውነቴ ጋር ተስማምተው እንዲያመሰግኑህ አንደበቴን በመንፈስ ቅዱስ ቋንቋ ቀርጸው። አስተውዬም ሳይገባኝም ለሰጠኸኝ ሁሉ ቦታ ሰጥቼ አመሰግን ዘንድ የመልአከትን ፍቅር አድለኝ" ብላችሁ ስትነሱ በቃ፤ ፍቅሩ በአጥንታችሁ ይዘልቃል። ደስታውና ኃይሉ በሕይወታችሁ ይገኛል። እረፍት ታገኛላችሁ። አሁን በእርግጠኝነት ይሄን ጽሑፍ ስታነቡ በራሱ ፍቅሩ በሆነ ደረጃ ይሰማችኋል።

ስለዚህ ዘወትር ስትጸልዩ ይሄንን ልዩ ፍቅሩን ያዙ።

ሐዋሪያት የክርስቶስ ፍቅር ልባቸው ላይ ቢታተም ግዜ፤ ኃይሉና ጸጋው ከልባቸው ወደ ውጪያዊ ሰውነታቸው፤ ከሰውነታቸው ወደ ልብሳቸው፤ ከልብሳቸው ወደ ጥላቸው ተጋብቶ፤ ጥላቸው ክብሩን ይገልጥ ጀምር። ድዊያንን ይፈውስ ነበረ። አጋንንት ያወጣ ነበረ። (የሐዋርያት ሥራ 5፥15)

የእኛም ጸሎት ከልባችን በጀመረው የእግዚአብሔር ፍቅር ላይ ከቆመ፤ ከልባችን ወደ ሰውነታችን ከሰውነታችን ወደ ሕይወታችን ተጋብቶ የሚታይ በረከትና ኃይል መገለጥ ይጀምራል። አጋንንትም ሊቋቋሙን ይቸገራሉ። በሌሎችም ዘንድ ተደማጭና ክብሩን የገለጥን እንሆናለን። በዓለም ፊት ሞገሳችን ይነበባል። "ክርስቶስ ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?" የሚለው የኃይል መገለጥ በሕይወታችን ውስጥ ጥቂት ጥቂት እያለ መገለጥ ይጀምራል። ይሄ ድንቅ ቸርነቱ ነው።

### 4.4) የጸሎት መርሃ ግብርና ሰዓታት

በመሠረቱ የሰው ልጅ 24 ሰዓታቱን ሁሉ ጸሎት ማድረስ ይችላል። በዚህ ሰዓት አትጸልዩ የሚል ገደብ ክርስትና ውስጥ የለውም። ነገር ግን በዓለም ስንኖር የሥጋ ኑሮአችን ሁኔታና አጋጣሚዎች የየቀኑን ሰዓታት በተለያየ ምክንያት ይይዙታልና ቤተክርስቲያናችን ለምዕመናኖቿ የጸሎት መርሃ ግብርና ሰዓታትን በሰማያዊ ምክንያት ቀርጻ አሰናድታ አቀርባለች። መነሻ ምሪቷም እንዲህ የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይሆናል።

"ስለ ጽድቅህ ፍርድ ሰባት ጊዜ በቀን አመሰግንሃለሁ።" (መዝሙረ ዳዊት 119፥164)

ይህን የልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊትን ቃል ስንመለከት በቀን ሰባት (7) ጊዜ የሰው ልጅ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን መታዘዙን ያመለክታል። ይኸውም በቅድስት ቤተክርስቲያናችን ሰባቱ የጸሎት ጊዜያት በመባል ይታወቃሉ።

በቅድስት ቤተክርስቲያናችን ትእዛዝ መሠረት ክርስቲያን በቀን ሰባት ጊዜ ጸሎት ማድረስ ይኖርበታል። በጣም በሚገርምና በሚያሳዝን ሁኔታ ይሄ ትእዛዝ የተላለፈው ለመነኮሳት ነው የሚሉ አሉ። ይሄ አረማዊያን አገልጋዮችና በሥጋ መፍትሔዎች ላይ ለረጅም ዘመናት የቆዩ የቤተእግዚአብሔር ሰዎች ቋንቋ ነው። የዳዊት ቃል ለቤተክርስቲያን ምዕመን እና አገልጋዮች ሁሉ የተሰጠ እንጂ፤ ለመነኮሳትና ለጻድቃን የተላለፈ አይደለም። የሐዲስ ኪዳኑም ቃል "ትጉና ጸልዩ" ነው የሚለው።

ሰባቱ ጸሎተ ሰዓታት ከቀኑና ከማታው ሦስት፣ ስድስት፣ ከቀኑ ዘጠኝና ዐሥራ አንድ ሰዓት ናቸው።

### 4.5) የጸሎት ሰዓታት

ለሊት 11:00 ☞ ውዳሴ ማርያም፣ ሰይፈ መለኮት፣ ሰይፈ ሥላሴ የዘወትር

ጠዋት 3:00 ☞ መልክአ ገብርኤል፣ መዝሙረ ዳዊት፣ አርጋኖን

ቀትር 6:00 ☞ መልክአ ሚካኤል፣ መልክአ ሥላሴ

ቀን 9:00 ☞ መልክአ መድኃኒዓለም፣ መልክአ ዑራኤል

ከሰዓት 11:00 ☞ ውዳሴ ማርያም፣ ሰኔ ጎለጎለታ፣ የምሕላ ጸሎት፣ መልክአ ፋኑኤል

ማታ 3:00 ☞ አርጋኖን፣ መልክአ ሩፋኤል

እኩለ ለሊት 6:00 ☞ መልክአ ሥላሴ፣ መልክአ ሚካኤል፣ መዝሙረ ዳዊት

### 4.6) ሰባቱ የጸሎት ሰዓታትና የሚጸለዩበት ምክንያቶች

1) **ነግሕ፦** ጠዋት11:00 ሰዓት ወይንም (በፈረንጆቹ 5:00 AM)

**የሚጸለዩት ጸሎቶች ፦ ውዳሴ ማርያም፣ ይዌድስዋ መላእክት፣ ሠይፈ ሥላሴ፣ ሠይፈ መለኮት**

✿ ጠዋት 11:00 አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔርን አምላክን በጸሎት የሚያመሰግንበት ምክንያት (ሚስጥር)

✓ እግዚአብሔር አምላክ ሌሊቱንና ጨለማውን አሳልፎ ብርሃን እንድናይ ስላበቃን በዚህ ሰዓት እግዚአብሔር አምላካችንን እናመሰግናለን። አንድም በዚህ ሰዓት ጌታችን ለክስ ከጲላጦስ ፊት ቀሞ የተወቀሰበት ሰዓት ስለሆነ፤ በዚህ ሰዓት አባታችን አዳም ያልተፈቀደለትን ዕፀ በልቶ ከገነት የተባረረበት ሰዓት ስለሆነ፤ ክርስቲያን ይህን ሁሉ እያሰበ ወደ አምላኩ እንዲጸልይ ታዝዋል።

2) **ማለዳ፦** ጠዋት 3:00 ሰዓት ወይንም (በፈረንጆቹ 9:00 AM)

**የሚጸለዩት ጸሎቶች ፦ አርጋኖን፣ መልክአ ገብርኤል፣ መዝሙረ ዳዊት**

✿ ሰልቱ ሰዓት ከጠዋቱ 3 ሰዓት አንድ ክርስቲያን እንዲጸልይ የታዘዘበት ምክንያት (ሚስጥር)

✓በዚህ ሰዓት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብስራት ገብርኤልን የሰማችበት ሰዓት ስለሆነ፤ አንድም በዚህ ሰዓት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችንን የጸነሰችበት ሰዓት ስለሆነ፤ አንድም ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጲላጦስ ፊት ቀርቦ የተገረፈበት ሰዓት ስለሆነ፤ እያንዳንዱ ክርስቲያን ይሄንን የመሳሰሉ ሁሉ እያሰበ እግዚአብሔር አምላኩን እንዲያመሰግን ታዝዋል።

3) **ጊዜ ቀትር፦** ቀን 6:00 ሰዓት ወይንም (12:00 PM በፈረንጆች)

**የሚጸለዩት ጸሎቶች ፦ መልክአ ሚካኤል፣ መልክአ ሥላሴ**

✿ አንድ ክርስቲያን እኩለ ቀን 6 ሰዓት ሲሆን እንዲጸልይ የታዘዘበት ምክንያት ወይም (ሚስጥር)

✓ ጌታችን በቀራኒዮ አደባባይ በመስቀል ተሰቅሎበታልና፤ አንድም ልብሱን ተገፎበታል፤ አንድም 'ሳዶር አላዶር ዳናት ሮዳስ' በተባሉ ችንካሮች ተቸንክሮበታልና፤ በሌላም ቅዱስ ሚካኤል በዚህ ሰዓት ክፉ መናፍስትን አሸንፎ ጥሎበታልና አንድ ክርስቲያን ይህን ሁሉ እያሰበ በዚህ ሰዓት እንዲጸልይ ታዞበታል።

4) **ተሰዓት፦** ቀን 9:00 ሰዓት ወይንም (3:00 PM በፈረንጆች)

**የሚጸለዩት ጸሎቶች ፦ መልክአ መድኃኔዓለም፣ መልክአ ዑራኤል**

✿ ተሰዓት ከ ቀኑ 9:00 ሰዓት ሲሆን አንድ ክርስቲያን የሚጸልይበት ምክንያት (ሚስጥር)

✓ አይሁዶች ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መራራ ሐሞት አጠጥተውበታል፤ አንድም ቅድስት ነፍሱን ከክቡር ሥጋው የለየበት ሰዓት ነውና፤ አንድም በመስቀል እንዳለ ሰባቱን አፅርሐ መስቀል የተናገረበትና ቅዱስ ዑራኤል ከጎኑ ውጋት ደም በዋንጫ ቀድቶ ዓለም ላይ የረጨበትም ነውና፤ በዚህ ሰዓት ይህንን እያሰበን እንዲጸልይ ታዝዋል።

5) **ሰርክ፦** ቀን 11:00 ሰዓት ወይንም (5:00 PM በፈረንጆች)

**የሚጸለዩት ጸሎቶች ፦ መልክአ ፋኑኤል፣ ውዳሴ ማርያም፣ ሰኔ ጎለጎታ፣ የሠርክ ጸሎት፣ የምኅላ ጸሎት**

✿ የሰርክ ሰዓት ከቀኑ 11፡00 ሰዓት አንድ ክርስቲያን እንዲጸልይበት የታዘዘበት ምክንያት ወይም (ሚስጥር)

✓ ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ከርሰ መቃብር የወረደበት ሰዓት ስለሆነ፤ አንድም ቀኑን በሰላም አሳልፎ ወደ ምሽት በሰላም ያደረሰን አምላክ ምስጋና ስለሚገባው ይህንን የመሳሰሉ ሁሉ ሕዝበ ክርስቲያን እንዲያስቡ ታዝዋል።

6) ጸለፀተ ንዋም፦ ማታ 3:00 ሰዓት ወይንም (9:00 PM በፈረንጆች)

የሚጸለዩት ጸሎቶች ፦ አርጋኖን፣ መልክአ ሩፋኤል

✿ ከምሽቱ 3 ሰዓት በዚህ ሰዓት አንድ ክርስቲያን እንዲያመሰግን የታዘዘበት ምክንያት (ሚስጥር)

✓ በዚህ ሰዓት እራሱ ጌታችን መድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ስርዓተ ጸሎት አሳይቶበታልና፤ አንድም በዚህ ሰዓት ጌታችንን አይሁድ በይሁዳ ጠቋሚነት ተረበርበው የያዙበት ሰዓት ስለሆነ፤ አንድም በዚህ ሰዓት አንድ ክርስቲያን ከመተኛቱ በፊት በሰላም ያዋለንንና ያስመሸንን አምላክ አመስግኖ መተኛት አለበትና ይህን ሁሉ እያሰበ እንዲጸልይ ታዝዋል።

7) እኩለ ለሊት፦ ሌት 6:00 ሰዓት ወይንም (12:00 AM በፈረንጆች)

የሚጸለዩት ጸሎቶች ፦ መዝሙረ ዳዊት፣ መልክአ ሥላሴ፣ መልክአ ሚካኤል፣ ሰይፈ ሥላሴ ዘወትር

✿ መንፈቀ ሌሊት ከሌሊቱ 6 ሰዓት በዚህ ሰዓት አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔር አምላኩን እንዲያመሰግንበት የታዘዘበት ምክንያት (ሚስጥር)

✓ በዚህ ሰዓት ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶበታልና፤ አንድም ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስና መቃብርን ድል አድርጎበታልና(ተነስቶበታልና)፤ በመዝሙረ ዳዊት አመሰግንህ ዘንድ በመንፈቀ ሌሊት እነሳለው ባለውም መሠረት ለምስጋና እንቆማለን።

### 4.7) በሥራና በአስገዳጅ ሁኔታ የተወጠረን ሰዎች ምን እናድርግ?

የአኗኗራችን ሁኔታና ጉዞ ምናልባት ሰባቱንም የጸሎት ሰዓታት ለመጠበቅና በጸሎት ቤት አምልኮታችንን በተገባ ለማከናወን የማንችልበት ምክንያት ይኖረናል።

ግን ልብ አድርጉ። የሚከተለው አማራጭ የተዘጋጀው ለጸሎት መቆም ለማይችሉ አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ላሉ እንጂ፤ የምንችል ሰባቱንም የጸሎት ሰዓታት ላይ መንበርከኩ ለራሳችን ነው በረከቱና ጥቅሙ።

ምንም ነገር፥ ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር ፍቅር ይነሣል የሚባለው ለዚሁ ነው። ከልቡ፣ ከነፍሱና ከአሳቡ እግዚአብሔርን የወደደ መንገድ አለው። የይስሙላ ፍቅርን የያዘ ሰበብ አለው።

እግዚአብሔር የልብ ፍቅራችንንና ከውስጥ አውጥተን የምንሰጠውን ንጹሕ መባዕ እንጂ፤ መመቸት አለመመቸቱን የሚመዝን የሁኔታዎች አምላክ አይደለም። እነሆስ፤ ፍቅራችሁን ሁሌ እንደገና እንደገና ፈትሹ። አድሱም።

ምናልባት ሥራ ላይ፣ ትምህርት ላይ ወይንም ሌላ ጉዳይ ላይ የጸሎት ሰዓት ቢደርስ ባለንበት ቦታ ሆነን ከቻልን ወደ ምሥራቅ ዞረን፤ ያልቻልን እዛው ሆነን፤ የሰዓቱን ጸሎት የቻልን ተንበርክከን ያልቻልን እንደሆነልን ሆነን ማድረስ።

በምሳሌ፦ ቀን 6:00 መልክአ ሚካኤል ይነበባል። ስለዚህ በሰዓቱ ጸሎት በተገባ ማድረስ የምንችልበት አጋጣሚ ከሆነ ፤ በእዝነ ሕሊናችን ለሊቀ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል እንጸልያለን።

< ቅዱስ ሚካኤል ሆይ፥ እርዳኝ! የኢጋንንትን ኃይል ገስጽልኝ፣ ርኩሳን መናፍስትን አስወግድልኝ፣ ታላቅ የሆነው ቅዱስ የሆነው ሰይፍህን በመሸጉብኝ ክፉ መናፍስት ላይ ጣለው፣ ሥልጣኑንም ሻረው፣ የበረከትህን ተሰፋና ኃይል ለኔም ስጠኝ፣ ከጎኔ ተሰለፍ፣ ውስጣዊ ሕይወቴን አጠናክር፣ በመንፈሳዊ ሀሳብህ አስበኝ፣ በምስጋና ሰፍራ ሁሉ በጸሎትህ አስበኝ።አባታችን ሆይ >

" ጊዜው መቼ እንዲሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፤ ጸልዩም።" (የማርቆስ ወንጌል 13፥33)

### 4.8) በቃል መያዝ ያለባቸው መዝሙረ ዳዊት ጸሎታት

(እስክትሸመድዱ በወረቀት ለየብቻቸው አስፍራችሁ መጠቀም ትችላላችሁ።)

ምግብ ሲበላ፣ የዕለቱ ጸሎት ሲጀመር፣ መንገድ ሲኬድ፣ የመልአክትን እርዳታ ስንጠይቅ መዝሙር 22/23'ን ጸልየን እንጀምራለን።

ደንቃራ ሲጥሉብን፣ መተት ሲልኩብን፣ ሱሉስ የመንፈስ ዝውውር ተደርጎ ሲገጥመንና መናፍስት ዙሪያችንን እንዳጠበቡ ሲሰማን መዝሙር 90/91'ን ጸልየን የተጣለውን ደንቃራ ወይንም ሱሉስ በእሳት እናቃጥለዋለን። ቦታውንም ጠበል እናስረጨዋለን።

ስለዚህ በተለይ መዝሙር 22(23)'ን እና መዝሙር 90(91)'ን በቃል መያዝ ያስፈልገናል። ሌሎቹንም የዳዊት መዝሙራት በደንብ መረምሩ።

### 4.9) በቃል የሚያዙ መዝሙራት

መዝሙር 14/15 ☜ የእግዚአብሔርን እውነት ስንናገር

አቤቱ፥ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል? በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል? በቅንነት የሚሄድ፥ ጽድቅንም የሚያደርግ፥ በልቡም እውነትን የሚናገር። በአንደበቱ የማይሸነግል፥ በባልንጀራው ላይ ክፉትን የማያደርግ፥ ዘመዶቹንም የማይሰድብ። ኃጢአተኛ በፊቱ የተናቀ፥ እግዚአብሔርንም የሚፈሩትን የሚያከብር፥ ለባልንጀራው የሚምል የማይከዳም። ገንዘቡን በአራጣ የማያበድር፥ በንጹሑ ላይ መማለጃን የማይቀበል። እንዲህ የሚያደርግ ለዘላለም አይታወክም።

መዝሙር 22/23 ☜ የዘወትር ጸሎት

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም። በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል። በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው። ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።

መዝሙር 40/41 ☜ ቸርነቱን ለመጠየቅ

ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ምስጉን ነው፤ እግዚአብሔርበክፉ ቀን ያድነዋል። እግዚአብሔር ይጠብቀዋል፥ ሕያውም ያደርገዋል፥ በምድር ላይም ያስመሰግነዋል፥ በጠላቶቹም እጅ አያሳልፈውም። እግዚአብሔር በደዌው አልጋ ሳለ ይረዳዋል፤ መኝታውን ሁሉ በበሽታው ጊዜ ያነጥፍለታል። እኔስ። አቤቱ ማረኝ፤ አንተን በድያለሁና ነፍሴን ፈውሳት አልሁ። ጠላቶቼም በላዩ ክፋትን ይናገራሉ። መቼም ይሞታል ስሙስ መቼ ይሻራል? ይላሉ። እኔን ለማየት ቢገባ ከንቱን ይናገራል፤ ልቡ ኃጢአትን ሰበሰበለት፤ ወደ ሜዳ ይወጣል ይናገራልም። በላዩ በመተባበር ጠላቶቼ ሁሉ ይሾካሾኩብኛል፥ በእኔ ላይም ክፋትን ያስባሉ። ክፉ ነገር መጣበት፤ ተኝቶአል ከእንግዲህ ወዲህ አይነሣም ይላሉ። ደግሞ የሰላሜ ሰው የታመንሁበት እንጀራዬን የበላ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ። አንተ ግን አቤቱ፥ ማረኝ እመልስላቸውም ዘንድ አስነሣኝ። ጠላቴ እልል አይልብኝምና ስለዚህ እንደ ወደድኸኝ አወቅሁ። እኔን ግን ስለ ቅንነቴ ተቀበልኸኝ፥ በፊትህም ለዘላለም አጸናኸኝ። ከዘላለም እስከ ዘላለም የእስራኤል አምላክ እግዚአሔር ይባረክ። አሜን አሜን።

መዝሙር 50/51 ☜ ምሕረቱን ስንማጸን

አቤቱ፥ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ። ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፥ ከኃጢአቴም አንጻኝ፤ እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፥ ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና። እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ፥ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ። እነሆ፥ እውነትን ወደድህ፤ የማይታይ ስውር ጥበብን አስታወቅኸኝ። በሂሶጵ እርጨኝ፥ እነጻማለሁ፤ እጠበኝ፥ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ። ሐሤትንና ደስታን አሰማኝ፥ የሰበርሃቸውም አጥንቶቼ ደስ ይላቸዋል። ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ፥ በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ። አቤቱ፥ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፥ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ። ከፊትህ አትጣለኝ፥ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ። የማዳንህን ደስታ ስጠኝ፥ በእሽታ መንፈስም ደግፈኝ። ለሕግ ተላላፎች መንገድህን አስተምራለሁ፥ ኃጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ። የመድኃኒቴ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ ከደም አድነኝ፥ አንደበቴም በአንተ ጽድቅ ትደሰታለች። አቤቱ፥ ከንፈሮቼን ክፈት፥ አፌም ምስጋናህን ያወራል። መሥዋዕትን ብትወድድስ በሰጠሁህ ነበር፤ የሚቃጠለውም መሥዋዕት ደስ አያሰኝህም። የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፥ የተሰበርውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም። አቤቱ፥ በውዴታህ ጽዮንን አሰማምራት፤ የኢየሩሳሌምንም ቅጽሮች ሥራ። የጽድቁን መሥዋዕት መባውንም የሚቃጠለውንም መሥዋዕት በወደድህ ጊዜ፥ ያን ጊዜ በመሠዊያህ ላይ ፍሪዳዎችን ይሠዋሉ።

**መዝሙር** 90/91 ☜ **ደንቃራን ለማፍረስ**

በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል። እግዚአብሔርን። አንተ መታመኛዬ ነህ እለዋለሁ፤ አምላኬና መሸሸጊያዬ ነው፥ በእርሱም እታመናለሁ። እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ ከሚያስደነግጥም ነገር ያድንሃልና። በላባዎቹ ይጋርድሃል፥ በክንፎቹም በታች ትተማመናለህ፤ እውነት እንደ ጋሻ ይከብብሃል። ከሌሊት ግርማ፥ በቀን ከሚበርር ፍላጻ፥ በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር፥ ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም። በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ፤ ወደ አንተ ግን አይቀርብም። በዓይኖችህ ብቻ ትመለከታለህ፥ የኃጥኣንንም ብድራት ታያለህ። አቤቱ፥ አንተ ተስፋዬ ነህና፤ ልዑልን መጠጊያህ አደረግህ። ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፥ መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም። በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና፤ እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል። በተኵላና በእባብ ላይ ትጫማለህ፤ አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ። በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ፤ ስሜንም አውቆአልና እጋርደዋለሁ። ይጠራኛል እመልስለትማለሁ፥ በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋራ እሆናለሁ፤ አድነዋለሁ አከብረውማለሁ። ረጅምን ዕድሜ አጠግበዋለሁ፥ ማዳኔንም አሳየዋለሁ።

**መዝሙር** 120/121 ☜ **ጥበቃውን ስንሻ**

ዓይኖቼ ወደ ተራሮች አነሣሁ፤ ረዳቴ ከወዴት ይምጣ? ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም፤ የሚጠብቅህም አይተኛም። እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም። እግዚአብሔር ይጠብቅሃል፥ እግዚአብሔርም በቀኝ እጅህ በኩል ይጋርድሃል። ፀሐይ በቀን አያቃጥልህም ጨረቃም በሌሊት። እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፥ ነፍስህንም ይጠብቃታል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔር መውጣትህና መግባትህን ይጠብቃል።

### 4.10) ምግብ ስንበላ ምን ብለን እንጸልይ?

በአብ

በወልድ

በመንፈስ ቅዱስ ስም (ሦስቴ)

ቅዱስ

አዶናይ

ኤልሻዳይ

ያሕዌ

ጸባዖት

ኢየሱስ

ክርስቶስ

አማኑኤል አሜን!!!

በቅዱስ ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም

በቅድስት እናትህ በእመቤታችን ድንግል ማርያም ስም

(የሌሎችንም ቅዱሳኑ ስም መጨመር)
(መዝሙረ ዳዊት ምዕ. 23)

1፤ እግዚአብሐር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።

2፤ በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።

3፤ ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።

4፤ በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል።

5፤ በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው።

6፤ ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአሐርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።

<< ማዕደ አብርሃምን የባረካችሁ አጋእዝተ ዓለም ሥላሴ ሆይ፥ የኔንም ማዕድ እንዲሁ ባርኩልኝ።

ጌታዬና አምላኬ ንጉሴም ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፥ በምድርም ሳለህ ለተከተሉህ ሁሉ በሰማያዊ ቃልህ ዓሳዎቹንና ቂጣዎቹን ባርከህና ቀድሰህ በብዙ እንዳጠገብካቸው፥ እኔንም እንዲሁ አድርግልኝ።

ለሥጋዬ የሆነውን ምግብ የሰጠኸኝ የሰማይ አባት ሆይ፥ ለነፍሴ ከሚሆነው ቅዱስ መብልህ እንዳልርቅ በመንፈስ ቅዱስ አጥር በፍቅርህ ከበበኝ።

ወደ ተራቡትም እሄድ ዘንድ፤ የተጠሙትንም እመለከት ዘንድ፤ ውስጤን አንተ በመለኮትህ ምሪት፣ በቸርነትህ ኃይልና በርኅራኄም ጸጋ ሞልተህ ያዘው። አሜን! >>

## ክፍል - 5

## የአምላክ ስግደት

### 5.1) የተረሳው ትልቁ እና ኃይለኛው ስግደት

በቅድስት ቤተክርስቲያናችን ከሚታወቁት ከአራቱ ስግደታት የመጀመሪያውና ኃያሉ ስግደት ይህ ስግደት ነው። የአምላክ ስግደት። የአምልኮት ስግድት።

ይህ ስግደት የሚሰገደው በልዩ ሦስትነቱ በመለኮታዊ አንድነቱ ለምናመልከው ለእግዚአብሔር ብቻና ብቻ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ዓለምን አስቀድሞ ስለኖረ ሕላዌነቱ፣ ዓለምንም ስለመፍጠሩ፣ ዓለምንም አሳልፎ ስለመኖሩ፣ ከሁሉ በላይ ያለ አንድ አምላክ ስለመሆኑ፣ ሁሉ ከእርሱ በእርሱ ለእርሱ ሰለመሆኑ፣ ስለ ባህሪይ ፈጣሪነቱ ፍጥረት ሁሉ ይገዛ ዘንድ ይገባዋል። የቀደመውን የሕግ ትእዛዝ በአንክሮ እናስተውል።

" አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ #ጌታ_አምላክህን_ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።" (የማርቆስ ወንጌል 12፥30)

ታላቂቱና የቀደመቺው ትእዛዝ ይህቺ ናት። ፍጥረታት ሁሉ ከዚህች ትእዛዝ ይነሣሉ። የሰው ልጆች የመጀመሪያ ትልቂቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህም፥ በፍጹም አሳብህም ውደድ።

መውደድን ከምን አስነሥቶ ጠቀመ? ከልብ። መውደድ ከልብ ይጀምራል። ዘወትር በሄድንበትና በቆምንበት ሁሉ፣ በሆነልንና በማይሆንልንም ልክ፣ ከውስጣችን አምላክን ማፍቀር ከልብ መውደድ ነው። ይህ የልብ መውደድ ወደ ነፍስ ይሄዳል። 'እኔ' እንተውና 'እርሱ' እንላለን። 'ከእርሱም ለእርሱ' እንላለን። እስከ ጥልቅም መሰዋትነት እናፈቅረዋለን። በመጨረሻው በፍጹም አሳብህ ይላል። አሳብ ታዲያ በሕሊናችን ጓዳ ተጸንሶ ወደ ውጪ የሚወለድ ግልጽ ውጤት እንጂ ተጨንግፎ የሚቀር ብቻ መሆን አይገባውም። መገለጥ ይገባዋል። መታየት ይገባዋል። መተግበር ይገባዋል።

እነሆም ከልባችን አስጀምረን፤ በነፍሳችን አኑረን በአሳባችን የምንይዘው ፍቅር የሚታየው በምግባራችን ብቻና ብቻ ነው። የሚጨበጠው ሲተገበር ነው። የሚኖረውም ሲተገበር ነው። እውነታነቱም የሚታየው በማድረግ ሲገለጥ ነው። ማውራትማ ሁሉ እንደበት ያለው ይችላል። "እወዳለሁ" ማለትማ ቀላል ነው። መናገርማ ያልወደደም እኮ ይችላል። ከልቡና ከነፍሱ የወደደ፤ ለይስሙላ ከወደደው እንኪያስ ከተግባር ውጪ በምን ይለያል?

የአምልኮት ስግደት፤ አንዱ ታላቅ የፍቅራችን መግለጫ፣ የመገዛታችን መታያ፣ የአክብሮታችን ውጤት፣ የተፈጥሮአችን ዓላማ፣ የጸጋችን መነሻ፣ የሞገሳችን ምንጭ፣ የኃይላችን መገኛ፣ ዲያቢሎስን ማሸነፊያ፣ በጠቅላላው እንደ እስትንፋስ የክርስትና ማንተመ መኖሪያ ነው።

### 5.2) እጅግ የዘነጋነው ይህ ስግደት

በጣም በሚያሳዝነን ሁኔታ በዘመናችን ክርስቲያን የሆነ ይህንን የአምላክ ስግደት እስከመኖሩም የረሳ ጭምር፤ ብዙ እጅግ በጣም ብዙ ሰው ነው። የአምልኮት ስግደት ምን እንደሆነ የማያውቁ ሰንበት ተማሪያን፣ ዘማሪያን፣ ዲያቆናት፣ ቀሳውስትና አባቶች ጭምር በዘመናችን አሉ። ቃሉ ግን እንደዚህ ይላል።

"እኔ ሕያው ነኝ፥ ይላል ጌታ፥ ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል መላስም ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል ተብሎ ተጽፎአልና።" (ወደ ሮሜ ሰዎች 14፥11)

ጉልበት ሁሉ ነው ያለው። ጉልበት ሁሉ ለእግዚአብሔር ይንበረከካል። ለእግዚአብሔር መስገድ የአምልኮት ስግደት ነው የሚባለው። ለአምልኮት ፍጥረት ሲሰግድ ስለፍቅሩ ይንበረከካል። ለካህሊነቱ ይሰግዳል። ከሁሉ በላይ ስለሆነ ሕላዌው ይሰግዳል። ይኸው ነው።

የአምልኮት ስግደት ለአጋእዝተ ዓለም ሥላሴ ብቻ ነው የሚሰገደው። ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ እየተባለ ነው የሚሰገደው። መልክአ ሥላሴን ተመልከቱ። << ፴፫፤ ለአብራክኪሙ። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ሆይ፤ የፍጥረታትን ሁሉ አብራክ ለሚያሰግድ አብራካችሁ ሰላምታ ይገባል >> ይላል። ፍጥረታትን ሁሉ ሲል በሰማይ ያሉ ቅዱሳን መልአክትን ጭምር ነው። በምሳሌ መልክአ ገብርኤልን መመልከት ይቻላል። << ፳፱፤ ለአቁያጺከ። ገብርኤል ሆይ በሰማያዊ አምላክ ፊት ዘወትር ተንበርክከው ለሚሰግዱ ጉልበቶችህና አቁያጾችህ ሰላም እላለሁ >> ይላል። ቅዱስ ገብርኤልም ዘወትር የሚሰገደውን የአምልኮት ስግደት እንደሚሰግድ መልክአው ይናገራል። በቅዱስ ዑራኤልም መልክአ << ፲፯፤ ለአቁያጺከ። በአንድነቱና በሦስትነቱ ለሚሰገድለት አምላክ ስግደትን ለሚያስቀድሙ ለሁለቱ አብራኮችህና እሳታውያን አቁያጾችህ ሰላም እላለሁ >> ይላል።

የቅዱሳኑን መልክአ ብትመለከቱ ቅዱሳን ሁሉ እንደሚሰግዱ በጉልህ አስቀምጦ ይናገራል።

ከአምላክ ውጪ ይህ የአምልኮት ስግደት ለማንም አይሰገድም።

"ያን ጊዜ ኢየሱስ። ሂድ፥ አንተ ሰይጣን ለጌታህ #ለአምላክህ_ስገድ_እርሱንም_ብቻ_አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው።" (የማቴዎስ ወንጌል 4፥10)

ጌታችን ራሱም በሰማያዊ ቃሉ 'ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ' ብሎ የአምልኮት ስግደት የሚገባው ለእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ጠቁሞናል።

ይህን ስግደት የማይሰግድ ክርስቲያን በቀጥታ ቋንቋ አምላክ የለኝም እያለ ነው በምግባረ ሕይወቱ። "እርሱን አምልክ ስግደትም ስገድ" ብሎ ቃሉ ከተናገረ፤ ከዚህ ውጪ አልሰግድም ካልክ እንግዲያውስ ያለምንም ጥያቄና መልስ አልሰግድም ብሎ ወደ ምድር ከተጣለው የጨለማ ሠራዊት ጋር ኅብረት በውድም በግድም ፈጥረሃል ማለት ነው። ይህንን ሕዘበ ክርስቲያኑ በአጽንዖት ሊገነዘብ የግድ ነው። በቃ አማራጭ የለም። ሦስተኛ መንገድ የለም። እሳት ወይ ውኃ። ብርሃን ወይ ጨለማ። ግራ ወይ ቀኝ። ገልለተኛ ዓለም የለም። መሃል የሚባል ነገር የለም። በውድ ካልሰገድክ በግድ የሚያደቅህ ባለጋራ አለ። ያለ አምልኮተ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ጦር ዕቃ ደግሞ በምንም በየትም በማንም አታሸንፈውም። ይህንኑ መመሪያ ጌታችን እንዲሁ ሰጥቶናል።

<< ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ። >>

ሰይጣንን "ሂድ" ብሎ ከእርሱ እንዲርቅ ጌታችን ሲያዘው ዝም ብሎ አይደለም። አስከትሎ የማሸነፊያውን ቃል እንዲህ ሲል አስቀምጦት ነው። 'ለጌታ ለአምላክህ ስገድ።' ስለዚህ እኛም ከሕይወታችን፣ ከግዜያችን፣ ከአሳባችን፣ ከምግባራችንና ከዘመናችን ውስጥ የገባውን የተሰወረ ጠላት በተገለጠ የምግባር ስግደት "ከኔ ሂድ አንተ ሰይጣን" እያልን እንዋጋለን ማለት ነው።

ይኼ መሠረታዊና እጅግ ኃያል ስግደት ስለምን እንደተሸፋፈነ የሚገርም ጉዳይ ሆኖ እናገኘዋለን። ሁሉም ሊባል የጣቶች ቁጥር በቀረው መልኩ ባለዝና መምህራን፣ አባቶችና ብዙ ሰባኪያን ስለዚህ የአምልኮት ስግደት ሲያስተምሩ አይሰማም። ለምን?

በመሠረተ ክርስትና አስተምህሮትም ከትላልቅ የተዋረድ እርከን አንስቶ እስከታቹኛው የሥልጣን ደረጃ ውስጥ የዚህ ኃያል ስግደት ምንነትና እውቅና የተደበሰበሰ ጉዳይ ነው። ብዙዎች "ጸልዩ፣ ንስሐ ግቡ፣ ጸበል ተጠመቁ" ሲሉ ይሰማሉ። ስገዱ የምትለዋ ነገር ላይ ግን የተዋጠ ድምፅ ሲያሰሙ ይስተዋላል። ለምን?

በእርግጥ ከዘመን ነባራዊ ሁኔታ አንፃር፣ እውነተኛ የአምልኮትን ትምህርት ከማፈን ወይ ካለማወቅ አንፃር እና በዋነኝነት ዲያቢሎስ ከዓለማዊ እስከ ቤተእግዚአብሔር ድረስ እጁን አስረዝሞ ብዙ ስውር ጥቃቶችን ያደረሰበት የሕይወት ምስክርነት ለዚህ << ለምን >> መልስ ይሆናል። ይህ ኃያል ስግደት በእጅጉ ኃያልና ዲያቢሎስን የማሸነፊያው ቁልፍ ስለሆነ በቀላሉ መረጃው ሰው ጋር ያለመድረሱ አግባብ ከመናፍስት ደባና ከአረማውያን ሚስጢራዊ አሠራር ግንዛቤ በኩል ሲታይ ምንም የሚያስገርም አይሆንም።

### 5.3) የአምልኮት ስግደት ለምን ይሰገዳል

1ኛ. ለእግዚአብሔር መገዛታችንን እንገልጥበታለን። ከስሙ ብቻ እንደምንገዘበው "የማምለኪያ ስግደት ነው።' መልአክት ሳይቀር የሚገዙበት ስግደት ነው። አምላክ አለኝ ካልክ፤ ስለ ፈጣሪ ትንበረከክ ዘንድ ፍቅሩ ይገዛሃል። ስግደት የእምነት መገለጥ መነሻም

መድረሻም ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚነግረን ክርስቶስ ሲወለድ ሰብአ ሰገል ሰግደውለታል። ክርስቶስ ሲያርግም ሐዋሪያት ሰግደውለታል። የምሕረቱ ዘመን የክርስቶስ ጉዞ በስግደት ተነሥቶ በስግደት ነው ያለቀው።

2ኛ. ኃይል የመልበሻ ቁልፍ ነውና ይሰገዳል። የአምልኮት ስግደትን በፍቅር የሚሰግድ ማንኛውም ክርስቲያን፤ ውስጣዊ ኃይሉ የበረታ ይሆናል። ማስተዋል ያገኛል። ደስታ ያገኛል። ሰላምና እረፍት ያገኛል። ጸጋና ሞገስ ያገኛል። ጤናው ይጠበቃል። በረከቱ እያደገ ይሄዳል።

3ኛ. ርኩሳን መናፍስት ለመቋቋም ጉልበት እናገኛለን። ልብ በሉ። የዲያቢሎስ ሠራዊትና የሰው ልጆች የምንለይበት ትልቁ ድንበር የአምልኮት ስግደት ነው። ታውቀም ሆነ ሳይታወቅ በቤተእግዚአብሔር ሰዎች ጭምር የማይነገር እውነታ የዚህ ስግደት ኃይል ክፉውን መንፈስ ስለማሸነፉ ሚስጢር ነው።

ክፉ ኃይላት ከሰማይ የተባረሩት አንገዛም ብለው ነው። አንሰግድም ብለው ነው። አንወድቅም ብለው ነው።

ታዲያም የሰው ልጅ በወደቀው የጨለማው ሠራዊት ምትክ ክብሩን ለመውረስና ምስጋናውን ለማድረስ ሲፈጠር ይህንን ተከትሎ ነው። አንወድቅም ባሉት ሠራዊት ፋንታ እንወድቃለን የሚሉን፣ አንገዛም ባሉት ሠራዊት ፋንታ እንገዛለን የሚሉን፣ አንሰግድም ባሉት እብሪተኞች ምትክ የሚሰግዱ የሰው ልጆችን እግዚአብሔር አምላክ ፈጠረ። ጽልመተ መልአክ ወደ ዓለም እስከሠራዊቱ የወደቀበት ምክንያት ለፈጣሪ አልገዛም ብሎ ነው። ለአምልኮት ስግደት አልወድቅም ብሎ ነው። እኔ ራሴ አምላክ ነኝ ብሎ ነው። እንዲሰገድለት እንጂ ወደ እግዚአብሔር እንዲሰገድ በፍጹም አይፈልግም። ስለዚህ አስተውሉ ከክፉው የመለያ ሰነድ ነው የአምልኮት ስግደት። ስግደቱ በሕይወትህ ውስጥ ስፍራ ካለው ዲያቢሎስ ካንተ ጋር በአንድነት ለመገኘት ይቸገራል። አብሮ በአኗኗርህ መካከል ያደፈጠ ጠላት ካለም ስግደቱን በምትሰግድበት ግዜ ምልክት ይሰጥሃል። ስግደቱን ከኑሮህ ካራቅህ በአንፃሩ ዲያቢሎስ ተመቻችቶ ኑሮህ ውስጥ ኑሮ ይሆናል።

### 5.4) የአምልኮት ስግደት መቼ መቼ ይሰገዳል?

የአምልኮት ስግደት ማለት፤ ለአምላክ የሚሰዋ የምስጋና መስዋት ነው። የአምልኮት ስግደት ቃላት ምስጋና ናቸው። << ስብሐት ለአብ፣ ሃሌሉያ ለወልድ፣ ምስጋና ለመንፈስ ቅዱስ>> አይነት ናቸው ቃላቱ። የአምልኮት ስግደቶች ሁሉም የምስጋና እና የኃይል ቃላት ናቸው። <<አብ ንጉሥ ነው፣ ወልድ ፍቅር ነው፣ መንፈስ ቅዱስ እሳት ነው>> የሚሉት የኃይል ቃላት ናቸው።

ስለዚህ እግዚአብሔርን ከማመስገን በምንም መልኩ አናቋርጥም። ከጅምሩ የተፈጠርንበት ዓላማ ለማመስገን ነው። እንኪያስ የአምልኮት ስግደት የመፈጠራችን ግብ መምቻ ነው። አምላክ አለኝ የምንልበት ነው።

ነገ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ዛሬ ተቀደሱ የሚለው ትእዛዘ ቃል ውስጥ፤ ዛሬ የመቀደሻው ሚስጢር ስግደት አንደኛው ክፍል ነው። ዛሬ ካልሰገድክ፤ ነገ የሚጠብቅህ የእግዚአብሔር ድንቅ ነገር ሳይሆን የሰይጣን ክፉ ነገር ነው። እነሆ የአምልኮት ስግደት ዘወትር ከእሁድ እስከ እሁድ የሚሰገድ የየዕለት ስግደት ነው። በምንም ቀን አይቋረጥም።

በደንብ አስተውሉ። የዘወትር ውዳሴ ማርያም ላይ "ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ አንዲት ስግደት እሰግዳለሁ" ይላል። ጸሎቱ የዘወትር ከሆነ፤ እንግዲያው ለዘወትር እንዲሰገድ የሚያዘውን ስግደት መስገድ ነው።

ከአምልኮት ስግደት ውጪ ያሉት የንስሐ፣ የጸጋና የክብር ስግደታት ናቸው የማይሰገድባቸው ቀናት ያሏቸው። እነዚህም በሰንበት፣ በበዓለ ሐምሳና በግዝት በዓላት ይሆናል። የአምልኮት ስግደት ግን መቼም አይቀምም።

### 5.5) የአምልኮ ስግደት እንዴት ይሰገዳል?

ከሦስቱ የስግደት አይነቶች ከሆነው ሰጊድ አሊያም ወዲቅ የምንለውን ስግደት እንሰግዳለን።

<u>ምክንያቱም</u>

1ኛ. ሙሉ በሙሉ ወድቀን የአምልኮታችንን ፍቅር ለሥላሴ እንገልጥበታለን።

2ኛ. ስግደት አንዱ የዲያቢሎስ መውጊያ ኃያል መሳሪያ ነውና እየተቃወመ ያስቸገረን ጠላት 'በቃለ-ኪዳን' ጸሎት በማሳሰብ ግንባር ላይ አስረነው በምንሰግድበት ጊዜ ምንጣፋችን ላይ የቅዱስ ሚካኤልን ምስል ልክ ሰይፉ ላይ ወይንም ደርቀ የእንጨት መስቀል ላይ አሊያ የጸለይንበት ቅዱስ መጽሐፍ ላይ ግንባራችንን እያስነካ ስንሰግድ የክፉውን ኃይል እንሰብርበታልና።

### 5.6) የአምልኮት ስግደትን ምን ምን እያልን እንሰግዳለን

- ✓ ለአጋእዝተ ዓለም ሥላሴ የሚሰገድ
- ✓ አምልኮን የሚገልጽ
- ✓ መቼውንም የማይቋረጥ ስግደት ነው።

(ማስታወሻ 3X ማለት 3 ጊዜ በሉት እንደማለት ነው። ለምሳሌ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ 1. ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ 2. ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ 3)

**<u>የአምላክ ስግደት</u>**

እሰግድ ለአብ

እሰግድ ለወልድ

እሰግድ ለመንፈስ ቅዱስ

እሰግድ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ (3X)

ስብሐት ለአብ

ስብሐት ለወልድ

ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ

ምስጋና ለከ፦ አብ

ምስጋና ለከ፦ ወልድ

ምስጋና ለከ፦ መንፈስ ቅዱስ

ሃሌሉያ ለአብ

ሃሌሉያ ለወልድ

ሃሌሉያ ለመንፈስ ቅዱስ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ (3X)

ቅዱስ እግዚአብሔር ፣

ቅዱስ ኃያል ፣

ቅዱስ ሕያው ፣

**የ አ ም ላ ክ ስ ግ ደ ት**

ቅዱስ አዶናይ ፣

ቅዱስ ኤልሻዳይ ፣

ቅዱስ ያሕዌ ፣

**የአምላክ ስግደት**

ቅዱስ እብኖዲ ፣

ቅዱስ ትስቡጣ ፣

ቅዱስ ጸባኦት ፣

ቅዱስ ኢየሱስ ፣

ቅዱስ ክርስቶስ ፣

ቅዱስ አማኑኤል ፣

**ንቁ**

እስከዚች ግዜ ላደረሠን

በመለኮቱ ኃይል ለጠበቀን

ፍፁም ፍቅሩን ለሰጠን

ቸርነቱን ላበዛልን

በብርሃኑ መንገድ ለመራን

ኃጢአታችንን ለታገሠልን

በሥጋወ ደሙን ለባረከን

ለድንግል ማርያም ልጅ

ለልዑል እግዚአብሔር

ክብር ምስጋና ይግባው

ለዘላለሙ አሜን።

**በ ማ ለ ዳ ን ቁ**

## ክፍል - 6

## የንስሐ ስግደት

### 6.1) በደላችንን የምናጥብበት ስግደት

አስቀድሞ ንስሐ፦ ነስሐ-ተፀፀተ ካለው የተገኘ ሲሆን፤ ንስሐ ማለት በሠሩት ኃጢአት መፀፀት፣ ማዘን፣ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ መወሰን ማለት ነው። ንስሐ ከዘለዓለማዊ ፍርድ የሚያድን፤ ዘማዊውን እንደ ድንግል፤ ሌባውን መጽዋች የሚያደርግ በሬት ከተሠራው ኃጢአት ንጹሕ አድርጎ፤ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚያደርግ ታላቅ መንፈሳዊ ምሥጢር ነው ።

ብዙዎች የዘመናችን ክርስቲያኖች ታዲያ የሚያውቁት ስግደት የንስሐን ስግደት ነው። በሰሞነ ህማማትና በዕለተ ስቅለቱ ቅድስት ቤተክርስቲያን በመገኘት በዓመት ከ6'ቀን ላልበለጠ ጊዜ ብቻ መስገድን እናውቃለን። የአምልኮት ስግደት፣ የጸጋና የቅዱሳን ስግደት በክርስቲያኑ ልብና ሕሊና ውስጥ ደብዛቸው ከጠፋ ዘመናት አልፈዋል። አሁን አሁንማ፤ በዓመት አንዴም ከምንሰግዳት ስግደት እየቀረጥን እየቀረጥን ስግደት የሚባለው ኃያል የእግዚአብሔር ጦር ዕቃን አርቀን ከወረወርን ቆየን። በዚህ ምክንያት ወደ ልባችንና ወደ ቤታችን ጤናችንን፣ ሰላማችንን፣ ደስታችንን፣ ጸጋችንን፣ ዕድላችንን፣ ተስፋችንን፣ ገንዘብና እውቀታችንን የሚወረውርብን ጠላት መጣብን።

የንስሐ ስግደት የሚሰገደው ለጌታችን ለመድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ቃሉን ተመልከቱ።

(ወደ ዕብራውያን ምዕ. 2)

----------

16፤ የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም።

17፤ ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ፥ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን፥ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው።

ቃለ እግዚአብሔር በኋለኛው ዘመን በቃልነት ሕላዌው ሳለ ለአብርሃም በሰጠው ቃል ኪዳን መሠረት ከትውልዱ ዘር ተገኝቶ፤ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፤ ሥጋ ሆነ። ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በኛ አደረ። ይህንንም የጌታችንን የምሕረት ጉዞ ሲጠቅስ የመልአክትን ያይደለ የአብርሃም ዘር ያዘ እንጂ አለ። እነሆም ጌታችን የሕዝብን ኃጢአት ለማስተሰረይ የታመነ ሊቀ ካህን ሆነ። መድኃኒዓለም በክህነት የካህናትም ሊቅ ነውና የበደልን ስርየት ይቀበላል። ኃጢአትንም ያጥባል። ንስሐንም ይሰጣል። እነሆም አስተውሉ ትልቁን ንስሐ የምንገባው ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የምድር ካህናትም የጌታችንን ፈለግ ለማጽደቅ ንስሐችንን ይቀበላሉ። ለካህን ብቻ ተናዘን፤ በጌታችን ፊት በየግዜው ለንስሐ ጸሎትና ስግደት መውደቅ ካቃተን እንግዲያውስ በድጋሚ ልባችንን ልንፈትሽና ልንመረምር ያስፈልገናል።

### 6.2) የንስሐ ስግደት ለምን ይሰገዳል?

ጌታችን መድሃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ነው። አምላክ ነው። በተዋሕዶ የከበረ መለኮታዊ ባህሪያቱን ከሰበአዊ ባህሪያቶቻችን በፍቅር ያስጠጋ አምላካችን ነው። ስለዚህ እንደ ሰውነቱ፥ እንደ ሊቀ ካህንነቱ ንስሐን ይቀበላል። ቃሉ እንደዚህ ተጽፎ ይነበባል።

"ስለዚህ፥ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፥ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ፤" (ወደ ዕብራውያን 3፥1)

የካህናት ሁሉ ሊቅ ነው። ስለዚህ እንደ ነፍስ አባታችን የነፍሳችንን ጩኸት ያዳምጥ ዘንድ አለው።

እንኪያስ፥ ንስሐ አባት ማግኘት የማትችሉ በየአረብ አገራቱ ያላችሁ እህቶች፣ በየዳር ድንበሩ ያላችሁ ወታደሮች፣ በየማይመች ሁኔታ የተገኛችሁ ወገኖች ንስሐ አባት እስኪመጣ ብሎ መቀመጥ አይደለም። ንስሐችሁን ለክርስቶስ እየሰጣችሁ ጠብቁ። ሲሆን ሲሆን የምድራዊ ካህናት ቀኖናውም የሚያዘው ወደ ክርስቶስ እንድትሰግዱ ነውና የንስሐ ስገዱ።

ምናልባት ይህንን አጣመው የሚረዱ አይጠፉም። ምድራዊ ካህናት አያስፈጉም የሚል ነገር የለም። እጅግ ያስፈልጉናል። አንደኛ የቤተክርስቲያን የቀኖና ደንብ ነው። ቤተክርስቲያን ሥርአቱን ስታዘጋጅ ምዕመኑ ተከትሎ ይተገብረው ዘንድ ነው። በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል የሚለውን ቃል ማጽደቂያ ናቸው ካህናት። ሁለተኛ ምድራዊ ካህን ፊት መናዘዝ መጸጸት እንዲፈጠር ይሆናል። ልባችን ደንዳና ስለሆነ የምንሸማቀቀው የምናየው ካህን አጠገባችን በሚሆንበት ግዜ ስለሆነ ነውና። ስለዚህ ለምድራዊ ካህናት መናዘዝ የግድ ነው። ግን ለካህናት ተናዘን ብቻ መቀመጥ የለም። የተሰወሩ በደሎቻችንና የማናውቃቸው ኃጢአቶቻችን ሁሉ በየግዜው ለጌታችን ማስታወቅ ያስፈልገናል።

ጌታችን ብቻ አይደለም የሚገርማችሁ ንስሐ የሚቀበለው። ከመንበረ ጸባኦት ስር ያሉት ካህናተ ሰማይ ሱራፌል፣ እንዲሁ ደሞ አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖትም ካህን ናቸውና ንስሐ ይሰማሉ። ቅዱስ አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖትም የክህነት ማዕረግ ያላቸው ጻድቅ ናቸው። በንስሐ ጸሎታችሁ መካከል አስቧቸው።

ብዙ ክርስቲያን ለሥጋ ካህናት ተናዞ ቁጭ ይላል። ያ በቂ አይደለም። የሥጋ ካህናት የሥጋን ነው የሚያዩት። እያንዳንዳችን የተሰወረ ኃጢአት ባለቤቶች ነን። ያንን የተሰወረ ኃጢአት በመጠቀምም ነው ዲያቢሎስ ምሽጉን የሚሰራው። ስለዚህ መንፈሳዊያን ካህናትን ማሰብና ለእነርሱ ኃጢአትን በቋሚነት መናዘዝ ውሰጣችን ለተደበቀ ጠላት እንዳይመች ያደርገዋል።

### 6.3) የንስሐ ስግደት መቼ መቼ ይሰገዳል?

ይህንን ጥያቄ መመለስ ያለበት ንስሐውን የሚያደረገው ክርስቲያን ነው። እንደ በደላችንና እንደ ንስሐችን ሁሉ ልንሰግድ ይገባናል። ቢሆንልን ዘወትርም ከአምልኮ ስግደት በተጨማሪ ብንሰግድ መልካም በሆነ ነበረ።

☞ የንስሐ ስግደት በሰንበትና በግዝት በዓላት እና በበዓለ ሐምሳ ወቅት አይሰገድም!!

*አሁን ልብ በሉ!*

የአምልኮ ስግደት ብቻ ነው የማይቋረጠው።

በበዓላትና በሰንበት የማንሰግደው የንስሐ ስግድት ነው። ይህን ከልባችሁ ሰሌዳ አድማቃችሁ ጻፉ!

☞ የንስሐ ስግደት በአጽዋማትና በሱባዔ ወቅት፤ እንዲሁም ንስሐ በገባን ጊዜ በበረታ ይሰገዳል።

አሁንም ልብ በሉ!

የአምልኮት ስግደት አይቋረጥም። ሱባዔ ብንይዝ፣ ጾሞ ላይ ብንሆን፣ ንስሐ በገባንም ጊዜ ሁለቱንም ስግደታት እንሰግዳለን እንጂ አንዱ በአንዱ አይተኩም!

### 6.4) የንስሐ ስግደት ምን ምን እያልን እንሰገድ?

**የንስሐ ስግደት**

የንስሐ ስግደት ለሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ይሰገዳል።

" እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።"

(ወደ ዕብራውያን 4፥14)

## ክፍል - 7

## የቅዱሳን ስግደት

### 7.1) ኃያሉ የጸጋ ስግደት

የቅዱሳን ስግደት እግዚአብሔር አምላክ ለወደዳቸው፣ ለመረጣቸውና ላከበራቸው ሁሉ የምንሰግደው ከመንፈስ ቅዱስ ጸጋቸው የምንካፈልበት፣ የእምነት ኃይላቸውን የምናገኝበት፣ የሃይማኖት ታሪካቸውን እንደምሪት የምንይዝበትና እግዚአብሔር ያከበራችሁ እኛም እናከብራችኋለን የምንልበት ስግደት ነው።

"እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው?" (ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥33)

የቅዱሳን ስግደት ወደ ሁለት ይከፈላል። እነርሱም፦

1) የጸጋና

2) የክብር በመባል ይታወቃሉ።

#### 7.1.1) የጸጋ ስግደት

ይህ ስግደት ለተወደደች ለተመረጠች ለከበረች የጸጋ ሁሉ ባለቤት ለሆነች ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ የሚሰገድ ስግደት ነው።

(የሉቃስ ወንጌል ምዕ. 1)

----------

48፤ እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤

49፤ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን 'ብፅዕት' የምንለው በአንደበት ብቻ አይደለም። እርሱንማ ያልተቀበላትስ ይለው የለም ወይ? ስለዚህ በተግባር እንሰግዳለን። ስለ ፍቅሯ እንሰግዳለን። ስለ እናትነቷ እንሰግዳለን። ለጸጋዋ እንሰግዳለን። የሰው ልጆች ሁሉ ስለሚመኩበት ንጽሕነቷ እንበረከካለን። በማንም ያልሆነና የማይሆን የአሳብም የሥጋም ቅድስናዋን የርኩሰታችንን ዝገት እንዲመልስልን ወገናችን በሆነ ፍቅሯ እንመረኮዝበት ዘንድ እንሰግዳለን። ከፈጣሪ በታች ከፍጡራንም በላይ እያሉ በአፍ ብቻ አውርቶ መቀመጥ መወደድን አይገልጽም። ይልቁኑ እንደከበረች ቅድሰት ኤልሳቤት 'የጌታዬ እናት እመብርሃን ሆይ፥ እንግዲያውስ የሰላምታሽን ድምፅ በሰማሁ ጊዜ እነሆ ጤናዬ፣ ሰላሜ፣ በረከቴ፣ ሞገሴ፣ እውቀቴ፣ ቤቴና ቤተሰቤም ሁሉ በደስታ ዘለለ' ስንል በስግደትም እናመሰግናታለን።

እመቤታችን ድንግል ማርያም ለእርዳታና ለደስታ የምትፈጠን እናት ነች። እንኳንስ እየሰገዳችሁ በእንባ ተማጽናችሁ እንዲሁ ሰውን ለመርዳት የማትዘገይ ወላጅ ነች። በወንጌለ ሉቃስም በምሕረቱ መጀመሪያ ዘመን ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ነበረ የወጣቺው። ዛሬም ድረስ ለሰው ልጆች ምሕረት መፍጠን ያለች ክርስቶሰ መድኃኒዓለምም በፍቅር ያያት የከበረች እናቱ እናታችን ናት። እኛና እግዚአብሔር በአማኑኤል አንድነታችን አንድ ጋር ሆነን እናታችን የምንላት የደስታ ባለቤት ነች።

### 7.2) የጸጋ ስግደት ለምን ይሰገዳል?

1ኛ• ትውልድ ነንና እመቤታችንን እንደ ትውልድነታችን ብፅዕነት ነሽ ከምንልበት አንዱ ማመሰገኛ መንገዳችን የጸጋ ስግደት ነው።

2ኛ• እመቤታችን ከመርገመ ሥጋ እና ከመርገመ ነፍስ የተጠበቀች ስትሆን ርኩስ መንፈስ የማንነቷን ዶሴ እስኪጠፋበት ድረስ በመንፈስ ቅዱስ የታጠረች የጸጋ ባለቤት ነች። እነሆም ከዚህ የጸጋዋ ኃይል ታካፍለን ዘንድ፣ እንደ እናትነቷ ትጋርደን ዘንድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልም ትባርከን ዘንድ እንሰግዳለን፡

3ኛ• ደስ ይበልሽ የተባለች እናት ነችና፤ የደስታዋ ሞገስና በረከት ሁልግዜ አብሯት የሚኖር የፍስሐ ባለሥልጣን ናት። ለጸጋ ስግደት በተንበረከክን ግዜ እንደ ኤልሳቤጥ ሁሉ ሰላምዋ ይገባብናል እና ሕይወታችን በደስታ ይዘላል።

4ኛ• ከክፉ መናፍስት ወጥመድ እና አሠራር ሁሉ እመቤታችን በክንዷ ሰብስባ ስለምትታቀፈን፤ ርኩሳን ጠላቶችን ለመቃወም እንችል ዘንድ ኃይል እንድናገኝ የጸጋ እንሰግዳለን።

### 7.3) የጸጋ ስግደት መቼ መቼ እንስገድ?

ይህን ለወላዲተ አምላክ ባላችሁ ፍቅር ልክ እናንተ ክርስቲያኖች መልሱት። የዘወትር ውዳሴ ማርያም ላይ <<አምላክን ለወለደች ለእመቤታችን እሰግዳለሁ>> ይላል። ስለዚህ ፍቅሯ ያባከናችሁ ሁሉ ዘወትርም መስገዱ መልካም ነው።

እንደ ንስሐው ስግደት አጠቃላይ የቅዱሳን ስግደት በሰንበትና በዓለ ሐምሳ **አይሰገድም!** ከዚያ ውጪ ለቅዱሳኑ እንደፍቅራችሁ ልክ ስገዱ። እንደመውደዳችሁ መጠን ስገዱ። ምክንያቱም ከፍቅር ያስጀመርነው ስግደት ኃይሉ በመውደዳችን ልክ ነውና።

### 7.4) ምን ምን እያልን የጸጋን ስግደት እንስገድ?

✓ ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ ይሰገዳል

✓ እመቤታችንን ከልቡ ያፈቀረና በተግባርም የሚያከብራት ዘወትር ይሰግዳል። ከታች እንደምሳሌ 21 ስግደት ተቀምጧል። ከዚህ በላይ መጨመርና እየበረቱ መሄድ እመቤታችንን ከሚወድድ ሁሉ ይጠበቃል።

## <u>የጸጋ ስግደት</u>

ጸጋን የሞላብሽ ሆይ ደስ ይበልሽ

ጌታ ካንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ

ከሴቶች መካከል የተባረከሽ ነሽና ደስ ይበልሽ

የማኅጸንሽም ፍሬ የተባረከ ነውና ደስታ ይገባሻል

የመድሃኒታችን እናቱ ላንቺ ደስታ ይገባሻል

በሰላምታ ደምፅሽ ተደስተናልና ደስታ ይገባሻል

የጸጋ ስግደት

ምስጋና ይገባሻል የእግዚአብሔር እናቱ ሆነሻልና

መደነቅ ይገባሻል ዓለምን የያዘውን ወልደሻልና

ብፅዕት ይገባሻል ለፀሐይ መውጫ ነሽና

የጸጋ ስግደት

መመስገን ይገባሻል ምሥራቅ ሆነሻልና

መደነቅ ይገባሻል መመኪያ ሆነሻልና

ብፅዕና ይገባሻል ለሃይማኖት መሠረት ሆነሻልና

ንግሥት የንጉሥ እናት

እመቤት የእግዚአብሔር እናት

ክብርት የአምላክ እናት

መቅረዝ የብርሃን እናት

ንጽሕት ጥኛ የንጭ በሬ እናት

ልዕልት በአርያም የሚኖር የልዑል እናት

ውድስት የምስጉን እናት

ምዕዝት የሽቱ እናት

የወርቅ ሣፅን የዕንቁ ባሕርይ መገኛ

ንቁ

በማለዳ ንቁ

## ክፍል - 8

## የቅዱሳን ስግደት

### 8.1) የክብር ስግደት

ሁለተኛው የቅዱሳን ስግደት ከጸጋ የእመቤታችን ስግደት በመቀጠል የሚገኘው የቅዱሳን ሁሉ ስግደት ነው። የክብር ስግደት በመባል ይታወቃል።

የክብር ስግደት እግዚአብሔር መርጦ ላከበራቸው ሁሉ ቅዱሳን የተገባ ስግደት ነው።

" ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፥"

(መዝሙረ ዳዊት 89፥3) እንዲል ልዑል እግዚአብሔር በመረጠው ሁሉ ላይ ኃይለ ቃልኪዳኑ በዚያ ይኖራል። ስለዚህ ለተከበሩት ቅዱሳን መልአክት፣ ጻድቃን ሰማእታት፣ ሐዋሪያት፣ ነብያት፣ ቅዱስ መስቀሉ፣ ቅዱስ ታቦትና ለሁሉ የእግዚአብሔር ቅዱስ በክብር እንሰግዳለን።

### 8.2) የክብር ስግደት ለምን ይሰገዳል?

✓ ቅዱሳን በእግዚአብሔር መንገድ ያለፉና ያሉ ናቸውና፤ የኛንም የሕይወት መንገድ ከእግዚአብሔር ጓዳና ጋር እንዲያስተባብሩልን እንማጸናቸው ዘንድ እንሰግዳለን።

✓ ቅዱሳን መላእክት በሰማይ ሠራዊት ሆነው የተገኙት አንድም ለማመስገን፥ አንድም እኛን ሊጠብቁ ነውና፤ ከረድኤተ ክንፋቸው ጥላ ውስጥ ገብተን እንጠበቅ ዘንድ እንሰግዳለን።

✓ ከቃልኪዳን ሰጦታቸው እንካፈል ዘንድ ለቅዱሳን እንሰግዳለን።

### 8.3)መቼ መቼ የክብር ስግደት እንሰግዳለን?

በምሳሌ የቅዱስ ሚካኤልን ስግደት እንመልከት። እነሆም መቼ መቼ እንሰገድ የሚለው ለቅዱስ ሚካኤል ባለን ፍቅር ይመረኮዛል። ዕለት ዕለትም መስገዳችን ታላቅ ነው።

እንደ ንስሐና ጸጋ ስግደታት ሁሉ በሰንበት እና በዓለ ሐምሳ ወቅት የክብር ስግደት #አይሰገድም። ከዚያ ውጪ ግን የቀን ገደብ የለውምና በፍቅራችሁ ልክ ለቅዱሳኑ ስገዱ።

ልብ በሉ፥ መቼውንም የአምልኮት ስግደት አይቋረጥም። ሦስቱ የንሰሐ፣ የጸጋና የቅዱሳን ስግደት ግን የማይሰገድባቸው ቀናት ሰንበት እና በዓለ ሐምሳ ይሆናሉ።

## ክፍል - 9

## መቁጠሪያ

መቁጠርያ በመሠረቱ ቃሉ 'መ-ቁ-ጠ-ር-ያ' ነው ራሱ ቃሉ። አባቶቻችን ማንበብ ስለማይችሉ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስን 41 ግዜ፣ በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስን 41 ግዜ፣ ኪርያላይሶን ክርስቶስ 41 ገዜ፣ አምላኬ አምላኬን 41 ግዜ፣ ሰምዓነ አምላክነ 41 ግዜ፣ አድኅነነ ከመዓቱ ይሰውረነ በምሕረቱ በእንተ ማርያም ወላዲቱን 41 ግዜ ይቆጥሩበታል።

በሁለተኛው መቁጠሪያ መግረፍያም ጭምር ነው። በጥንታዊቷ ቤተክርስቲያናችን ከሚገኙና ሰይጣን ዲያብሎስን ከምንዋጋበት መሳሪያዎቻችን መካከል አንዱ መቁጠሪያ ነው።

" በአንተ ጠላቶቻችን እንወጋቸዋለን በስምህም በላያችን የቆሙትን እናዋርዳቸዋለን " መዝ.43 (44) ፥5

መቁጠሪያ ለሰው ልጅ በጣም ከሚያስፈልጉት በጸሎት ጊዜያት ውስጥ አንዱ ነው። ምክንያቱም ከዛሬ መቶ ሃያ አመት በፊት የነበሩ አባቶች በመቁጠሪያ ጸሎት በመጸለይ ኃይለ አጋንንትን በመቀጥቀጥ ድል ያድርጉት፤ ሥጋቸውንም ለነፍሳቸው ያስገዙት ነበር። መናፍስት በሕይወታቸው ውስጥ እንዳይገባ ትከሻቸዉን፣ ጀርባቸዉን፣ ማጅራታቸዉን፣ ራሳቸዉን፣ እግራቸዉን፣ ባታቸዉን፣ ሆዳቸዉን፣ ክንዳቸዉን በመቁጠርያው ይመቱታል። ራሳቸውን የሚመቱት ጥልቅ የሆነ የመንፈሳዊ ሕይወት ግንዛቤ ስላላቸው ነው። የሚመቱት ክፉ መናፍስት ጸሎታቸዉን እንዳያስታጉል፣ ድካም እንዳያመጣባቸው፣ እግራቸዉን እንዳይይዝ፣ ቁርጥማት እንዳይሆን፣ የብርድ በሽታ እንዳይሆን፣ ነርቭ እንዳይሆን ግንዛቤ ስላላቸው ነው።

አሁን ግን ይሄ መንፈሳዊ ውጊያ ተረስቶ መቁጠሪያ ለቀራቢ ነው፤ መቁጠሪያ ለምንኩስና የበቁ ሰዎች ነው እየተባለ ይገኛል። ይህ ፍጹም ስህተት ነው ።

በመጽሐፍ ቅዱስ 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 9፥27 ላይ ያለውን ቃል እንመልከት።

"ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ። "

እየጎሰምሁ ሲል እየቀጠቀጥኩ ማለቱ ግልጽ ነው። ስለዚህም መቁጠሪያን በመጠቀም ከውስጥ ያደፈጠን ጠላት መያዝና ማቃጠል፥ ከሰውነታችንም እንዳይገባ ማስጨነቅ እና ማባረር እንችላለን።

### 9.1)መቁጠሪያን እንዴት እንጠቀምበት?

መቁጠሪያ በአጠረ አገላለፅ መንፈሳዊ ላብራቶሪ ነው። ውስጠኛ ክፍልህን በመንፈስ ይያዝ አይያዝ ትፈትሽበታለህ። ትለይበታለህ። ይህንን የመቁጠሪያን አገልገሎት ቀደምት በተለይም ከ60'ዎቹ ዘመን አስቀድመው የነበሩት አባቶቻችን በተገባ ያውቁታል። ከእነርሱም የእምነትና የታሪክ እውነት ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ ነው።

መቁጠሪያ ዲያቢሎስን ለመዋጋት እጅግ በጣም አስፈላጊ የክርስቲያን የጦር ዕቃ ነው።

አብዛኛውን የት የት ይቀመጣል መንፈስ የሚለውን ስናስተውል፦

✓ቀኝና ግራ ላይ ትከሻ

✓ማጅራት አከባቢ ከኋላ

✓አእምሮ እና ግንባር ላይ

በተጨማሪ ዓይን ላይና እንደዚሁም ክንድ ላይ፣ እጅ ላይ፣ እግር ላይ። ወደ ሌላ መንገድ ሊወስድህና ሊመራህ ሲፈልግ እግር ላይ ነው የሚቀመጠው።

በመቀራኘት አኗኗር ባህሪይ ልብ፣ ሕሊና፣ አእምሮ ላይ ነው የሚቀመጠው። ግለሰቡ የሚጸልይ ከሆነ ከዚህ ውጪ ባለ ክፍል ላይ ነው የሚቀመጠው። ጸሎት ከሌለ ግን ሕሊና፣ አእምሮ፣ ልቦና ላይ ነው የሚቀመጠው። በዚህ ግዜ ሕሊና ከነፍሳችን አንደኛው ክፍል ነው። ልቦናም ከነፍሳችን አንደኛው ክፍል ነው። ይህንን ተቆጣጠረው ማለት መቶ በመቶ ይዞታል ማለት ነው።

ዛሬ አብዛኛው በዚህ ውስጥ ነው ያለው። ስለዚህ እዚህ ልብ እና ሆድ ላይ በሚመታበት ግዜ መብላት፣ ማቃጠል፣ መውረር፣ መሯሯጥ የተለየ ባህሪያቱ ነው። መገለጫው ነው። በዚህ ግዜ አድፍጧል፣ ተቀምጧል፣ መኖርያ አድርጎታል ማለት ነው። አሁን በነዚህ እና መሰል ምልክቶች ያደፈጠውን ጠላት ለየው ማለት ነው በቃ። እንደመሸገ ነቃበት ማለት ነው።

ከዛ በኋላ ማዳከም የሚለው ቃል ተከታይ ይሆናል። በጸሎት ቦታ ላይ ማዳከም፣ እየገረፈው ማዳከም፣ ትእዛዝ እየሰጠው ማዳከም፣ "ጸጥ በል አትረብሸኝ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም አዝዤኻለው፣ በድንግል ማርያም ሥም አዝዤኻለው" ብሎ በመቁጠርያ ሲመታው የመፍራት ባህሪይ እየተሰማው ይመጣል። ጫን ያለ ምት ስንመታው እዚህ ሆድ አከባቢና ግራና ቀኝ ትከሻ፣ በማጅራት አከባቢ፣ ራስ ላይ ስትቀውረው ቶሎ ብሎ ነው የሚለቀው። ወደ ግንባር ላይ ውጣ ስንለው ልክ እንደሚንቀሳቀስ ነፍሳት ሆኖ ወደ ግንባር ላይ ሲወጣም ሊሰማን ይችላል። ከዛ በኋላ እዛ ላይ ታሰረዋለህ። ግንባር ላይ መታሰሩ ደግሞ ዋናው ጥቅሙ ምንድነው? አንተ የምታየውን አያይም። በተጨማሪ ግንባር ላይ አስረህ ስትሰግድና ስትጸልይ በጣም እየተዳከመ ይመጣል። "ከዓይን ውጣ ትለዋለህ፣ ከጀሮ ውጣ ትለዋለህ፣ ከልቤ ውጣ፣ ከአእምሮዬ ውጣና ግንባር ላይ ታሰር" ብለህ በመቁጠሪያ እየገረፍህ ስታዘው በመንፈስ ቅዱስ ዛንጅር ሄዶ ይታሰራል። አሁን ስትሰግድ አብሮ ይሰግዳል። አልሰግድም ብሎ የወደቀ መንፈስ ስለሆነ በዚህ ጊዜ በጣም ይቃጠላል። ከዛ በኋላ እንዲህ እየቀጠቀጥከው በመቁጠርያ ስታሰለቸው ከጥቂት ግዜ በኋላ ስለሚደክመው በልብህ ውስጥ፣ በሕሊናህ ወይም በጆሮህ ውስጥ መናገር ይጀምራል። "ከየት ነህ የመጣህው? የዘር ነህ? ፣ የቤተሰብ ነህ ? ከየት ነህ የመጣኸው ማን ነው የላከኽ?" ስትለው ለራስህ ይነገርሃል ሌላ ጠያቂ ሳያስፈልግ። በዚህ ግዜ በቂ መረጃ ከወሰድክ በኋላ አሁንም ቀጠቀጣውን እና በመንፈሳዊ ልምምድ ማዳከሙን ስትቀጥል እየከበደው ስለሚመጣ ራሱ ተነስቶ ይሄዳል ወይንም ከውስጥህ ሆኖ ሸኘኝ ይልሃል። እንግዲህ የመቁጠሪያ ጉልበት ይሄን ያህል ነው።

### 9.2) መቁጠሪያን ለመጠቀም

✔ ከገዛችሁት በኋላ በቤተክርስቲያን አባቶች አስባርኩት።

✔ ቤት ይዛችሁትም ስትመጡ ከጸሎት ቦታ ውጪ አታስቀምጡት

✔ በመቀጠል <<በስምህ በላያችን የቆሙትን እናዋርዳለን>> ነው የሚለው በስሙ ኃይል እንዲያገኝ፤ 41 ወይም 64 የአምልኮት ስገዱበት

✔ የዕለቱን ጸሎትና ምስጋና ካደረሳችሁ በኃላ በስመ መለኮቱ ባርኩት

✝ ቅዱስ አዶናይ

✝ ቅዱስ ኤልሻዳይ

✝ ቅዱስ ጸባኦት

✝ ቅዱስ ያሕዌ

✝ ቅዱስ ኢየሱስ

✝ ቅዱስ ክርስቶስ

✝ ቅዱስ አማኑኤል

✝ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም

✝ በቅድስት ሥላሴ ስም

✝ በጌታችን መድሃኒታችን በኢየሱስ መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ስም

✝ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስምና የቅዱሳን ስም ወዘተ...

<< የተባረከ ፣ የተቀደሰ ፣ እግዚአብሔርም የወደደው ፣ ኃይለ መለኮቱም ያረፈበት ፣ የጸጋውና ሞገሱ ክብር የተገለጠበት ፣ የዲያቢሎስንም ክንድ የሚሰበር ፣ እንደ መንፈስ ቅዱስ የእሳት ጅራፍ ይሁን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክብር አሜን >> እላዩ ላይ በእስትንፋስ እፍ ትሉና ትባርኩታላችሁ።

✓ በመቀጠል ጸሎት ቤት የሚቀመጥን ቢሆን ቅባዕ ቅዱስን ካልተገኘ እምነት ትቀቡታላችሁ።

### 9.3)በመቁጠሪያ ምን ምን እያልን እንቀጥቅጥ?

❖ ይህንን ለመመለስ ሕይወታችንን ማየት ነው። ከውስጥ ያደፈጠ ጠላት በሕይወታችን ምን ምኑ ላይ አጥቅቶናል? የሕይወታችን አኗኗር የቱ የቱ ላይ ተሰነካከለ? ምን ችግር ደረሰብን? የሚሉትን መሰል ጥያቄዎች አሰናስለን የመሸገውን ክፉ መንፈስ በስመ ኃይሉ መቀጥቀጥ ነው።

<u>ለምሳሌ፦</u> ☞ ያደፈጥክ የቤተሰብ ዛር ፣ መተት ፣ ዓይነጥላ ፣ ቡዳ ፣ ክፉ መንፈስ ፣ ርኩስ መንፈስ ፣ የአጋንንት ሠራዊት ፣ የሰይጣን ሠራዊት፥ ጤናዬን የምትነካ ፣ ሰላሜን የምታበላሽ ፣ ችግር የሆንክብኝ ፣ ጭንቀት የሆንክብኝ ፣ ደስታዬን የነጠክ ፣ ፍቅሬን የቀማህ ፣ ቤተሰቤን የበተንክ ፣ ዕድሌን የዘጋክ ፣ ትምህርቴን ያበላሸህ ፣ ስራዬን ያከሸፍክ ፣ ምቀኛ የሆንክብኝ ፣ በረከቴን የወሰድክ ፣ በሰውነቴ ውስጥ ያደፈጥክ ፣ በቤቴ ውስጥ የመሸክ ፣ በቤተሰቤ ውስጥ የተደበቅ ...ወዘተረፈ

የሥላሴ ስም ያንድድህ ፣

የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይቀጠቅጥህ ፣

የእመቤታችን ወላዲተ አምላክ ስም ያቃጥልህ ፣

የሊቀ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ስም ይሰርህ ፣

የብስራተ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ስም ሥልጣንህን ያፍርሰው ፣

በጸባኦት ፣ በአዶናይ ፣ በኤልሻዳይ ፣ በያሕዌ ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ፣ በአማኑኤል ስም ያደፈጥክ ሰይጣን ተቃጠል

በወላዲተ አምላክ ፣ በቤዛዊት ዓለም ፣ በቅድስት ኪዳነ ምሕረት ፣ በእናታችን ድንግል ማርያም ሰመ ጸጋ የተደበቅ አጋንንት ሥራህን ታቆማለህ

ሐሳቤ ውስጥ ሐሳብ የሆንክ ፣ አካላቴ ውስጥ አካል የሆንክ ፣ ተመሳስለክ የቀመጥክ ጠላት ፣ በመድሃኒተ ዓለም በኢየሱስ አምላክ ክርስቶስ ስም ተይዘሃል ...ወዘተ

እንዲህ እያላችሁ ስትቀጠቅጡት፦

1• ጀርባን መውረር ማሳከክ አሊያ የአንዳች ነገር መሯሯጥ

2• እንደ ድንጋይ መክበድና ስሜት አልባ መሆን

3• ልክ እንደ እሳት ማቃጠልና መብላት

4• አስቀድሞ ያልነበረ ሽፍታ ፣ ብጉር ፣ እብጠት ፣ ቁስል መውጣት

5• ቦታው ላይ ልክ ጸጉር የወጣበት ይመስል መጥቀርና ጥላሸት መልበስ

6• መቁጠሪያ ሲያዩ ፍርሃት ፍርሃት ማለት፣ መጨነቅ፣ መቁጠሪያ ላለመጠቀም ከውስጥ የራስ አሳብ የሚመስል ድምፅ መወትወት

እና ሌሎች ተመሳሳይ ምልክቶች ይታያሉ። እነዚህ ምልክቶች ሳትሰግዱና ሳትጸልዩ፥ በአምላክና ቅዱሳኑ ስም ሳትጠቀሙ ዝም ብላችሁ ብትቀጠቅጡት አይታዩም።

በመለኮት ስሞች፣ በእመቤታችን ስሞች እና በቅዱሳን ስሞች ከቀጠቀጥነው በኋላ፦

"ያደፈጥህ መንፈስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ግንባር ላይ ውጣና ታሰር፥ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ታስረሃል። በወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ስም ታስረሃል።" ብሎ ካዘዙ በኋላ ግንባርን የጸሎት መጽሐፍ፣ የቅዱስ ሚካኤል ምስልን አሊያ የእንጨት መስቀልን እያስነኩ <<በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የታሰረክ ጠላት አብረከኝ ስገድ>> ብሎ አዝዞ የአምልኮት ስግደት በሚሰገድበት ግዜ መንፈሱ መቋቋም አይችልም።

ቅዱስ ቃሉ እንደዚህ ይለናል < የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ> ኤፌሶን 6፥10-18

**ክፍል - 10**

## የጸሎት ቤት መርሃግብር

የጸሎት ክፍልን ካዘጋጀን በኋላ የጸሎት፣ የስግደትና የመቁጠሪያ ምግባራችን ቀጣዩ ጉዳይ ይሆናል። ስለዚህ እንዴት መንፈሳዊ ምግባርን በቀደም ተከተል እናድርግ?

1ኛ✓ መጀመሪያ ጸሎት ቤታችሁ (ትንሽዬ ቤተመቅደሳችሁ) ከመግባታችሁ በፊት ፊታችሁንና እጅ እግራችሁን ታጥባችሁና ንጹሕ ሆናችሁ ተዘጋጁ። ሕልመ ለሊት(ለወንዶች) ደመ ጽጌ(ለሴቶች) በሚሆንበት ወቅት ሙሉ ሰውነት ታጥባችሁ ቢሆን ነው መልካም።

ምክንያቱም፦ እግዚአብሔር ንጹሕ መስዋትን ይወዳልና። ቤተመቅደስ እንደ ክርስቶስ ሰርግ ቤት ክብርት ነችና።

2ኛ✓ ነጭ አልባስ ብትለብሱ መልካም። አሊያም ለቤተክርስቲያን ያዘጋጃችሁትን አልባስ። ቢጠፋ ቢጠፋ ግን ነጠላ አይጠፋም።

ምክንያቱም፦ ክርስቶስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ብሏልና ነጭ ብርሃንነቱን ወክለን በእኔ የሚመላለስ ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ያለውን የተስፋውንና የቃልኪዳኑን ቃል እንደዛለንና፤ ብርሃንነቱን በነጭ አልባስ እንገልጻለን።

3ኛ✓ እንደ ገባን በመቆሞ ልክ ከሥላሴ ስዕል ትይዩ እንሆንና ሦስት ጊዜ እናማትባለን። ካማተብንም በኋላ በቅዱሳን ስሞቹ ጸሎታችንና ስግደታችንን እንገርካለን። ለምሳሌ፦ እንደዚህ ተብሎ ይባረክማል!

ቅዱስ እግዚአብሔር

ቅዱስ ኃያል

ቅዱስ ሕያው

ቅዱስ አዶናይ

ቅዱስ ኤልሻዳይ

ቅዱስ ያሕዌ

ቅዱስ ጸባኦት

ቅዱስ ኢየሱስ

ቅዱስ ክርስቶስ

ቅዱስ አማኑኤል

በአብ ፣ በወልድ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም

በኢጋእዝተ ዓለም ቅድስት ሥላሴ ስም

በእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ስም (ሌሎች ቅዱሳንን መጨመር)

ብለን በሰዓቱ እና በግዜው ላደረሰን እና ላቀመን አምላክ ምስጋና ከማድረስ መጀመር።

4ኛ✓ በመቀጠል መዝሙር 22'ን መጸለይ ☜ የግድ በቃል መያዝ አለበት። በጣም አጭር ጸሎት ነው።

[ እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም። በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል። በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው። ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።]

5ኛ✓ አስከትለን በዛው "አባታችን ሆይ" እንላለን

6ኛ✓ ቀጥለን ከቆምንበት የሥላሴ ትይዩ ምስል ሆነን የአምልኮት ስግደት መስገድ።

7ኛ✓ ስንጨርስ ተንበርክከን የሰዓቱን ጸሎት

ማለትም ለምሳሌ ምሽት 3፡00 ከሆነ ጸሎተ አርጋኖን፤ ሌሊት 11፡00 ከሆነ ውዳሴ ማርያም ማድረስ።

8ኛ✓ በአባታችን ሆይ የሰዓቱን ጸሎት መዝጋት

9ኛ✓ የግል ጸሎታችንን ማድረስ (ርዕስ ሰጥተን የምናደርሰው ወይንም የምንጠይቀው የግል ጸሎት)

10ኛ✓ ጸሎቱን ካደረስንም በኋላ መቁጠሪያችንን አንስተን ከላይ በተገለጸው መለኮት ስሞቹ በመባረክ፤ በመቀጠል አሁንም ከላይ የተገለጹትን መለኮት ስሞችና የቅዱሳንን ስሞች እየጠሩ የመሸጉ ክፉ መናፍስትን ለመለየት ጀርባን፣ ሁለቱንም ትከሻዎች፣ ጭንቅላትንና ሆድን በእምነት መቀጥቀጥ። በተለይ ግን ጀርባን።

እንዲህ አድርገ በመቁጠሪያ ውስጣችንን ስንፈትሽ ምልክቶችን የምናገኝ ከሆነ የተደበቀውን ጠላት እንነቃበታለን።

መንፈስ በመቁጠሪያ ፍተሻ ምልክት ካልሰጠ ሦስት ምክንያት አለው።

❶• በሚስጢር የተላከ መተት፣ ቁራኛ፣ ቡዳና የዛር መንፈስ ከሆነ (ምልክት ላለመስጠት ይታገላል በሚስጢር የገባ ከሆነ)

❷• ለጊዜው ዘወር ያለ መንፈስ ይሆናል (ወጣ ገባ የሚል ከሰው የገባ የቡዳና የመተት መንፈስ ከሆነ)

❸• አምነንና ልባችንን ሰጥተን በተገባ የአምልኮ ልምምዱን እያደረግንም ካልሆነ ጠላት ምንም ለመኖሩ ፍንጭ አይሰጥም። ስለማያቃጥለው።

11ኛ✓ ስንቀጠቅጥ ምልክት ከሰጠን ቅጥቀጣችንን ለጊዜው እንተውና በቅባዕ ዘይት ግንባራችንን አመሳቅለን ሦስቴ ቀብተን ምልክት የሰጠው ጠላት ግንባር ላይ እንዲታሰርልን በጸሎት እንጠይቃለን። (በመለኮት ስሞቹም በሌሎቹም ቅዱሳን ስም ማሰር ይቻላል። የእምነት ጉዳይ ነው።)

እዚህ ጋር አንድ ነገር እናስተውል። ቃሉ የሚለው ስጡ ይሰጣችኋል ነው። እኛ የእግዚአብሔርን ስንሰጥ እግዚአብሔር ደሞ የኛን ይሰጠናል። አሁን ታሰር ብላችሁ በእምነት ከጠየቃችሁ በኋላ የተቀረው የሰማይ ጉዳይ ነው። የእናንተ ድርሻ ግማሹን መሙላት ነው። የተቀረው እኛን ለማዳን የሚችኩሉት የሰማይ ኃይላት ጉዳይ ነው። ስለዚህ የሰማይ ጊዜውን ለሰማይ ተዉት።

ሌላው እራሱ መንፈሱም ከውስጥ ታሰሬያለሁ ሊላችሁ ይችላል። ማድመጡ አያስፈልግም። በቃ እርሱን ወደ ጎን ትታችሁ ዝም ብላችሁ ለእግዚአብሔር በእምነት የሚሰጠውን ብቻ ስጡ።

12ኛ✓ በመቀጠል የአምልኮት ስግደት ስገዱ። ግንባር ላይ ስላሰርነው፤ ግንባራችንን የእንጨት መስቀል ላይ አሊያ ቅዱሳን ስዕላት ላይ ወይንም ጸሎተ መጽሐፍ ላይ እያስነካን ስንሰግድ በጣም ይቃጠላል። አስቀድሞ ከሰገድነው የአምልኮ ስግደት ይሽኛው የሚለየው ይሄ መንፈሱን ካዳከምን በኋላ 'አብረኸኝ ስገድ 'ብለን ትእዛዝ ሰጥተን ስለምንሰግድ ነው። ከዚህ በኋላ ድጋሚ በመቁጠሪያ ስትነርቱት ስለታሰረ በጣም ኃይልና አቅሙን እያደከማችሁበት ትመጣላችሁ።

13ኛ✓ ጸሎታችንንና ስግደታችንንም ተቀበለን ብለን እንጸልይና በአባታችን ሆይ እንዘጋለን።

☞ ተጨማሪ በዛው የንስሐና የቅዱሳን የሌሎችንም ጸሎታት የምናቀርብ ከሆነ ጸሎቱን ሳንዘጋ እንቀጥላለን።

ለምሳሌ፦ ቀኑ 19 ከሆነ ከአምልኮ አስከትለን 6ኛው ቅደም ተከተል ላይ ተመልሰን ለቅዱስ ገብርኤል የክብር እንሰግዳለን። ከዛ 9ኛው ቅደም ተከተል ላይ ስንደርስ የግል ጸሎታችንንም እናቀርብለታለን።

☞ ይህ የዘወትር የአምልኮ የቤት ውስጥ ቅዱስ መንፈሳዊ ልምምድ ነው። በተለይ ይህንን ልምምድ ከማድረጋችሁ አስቀድሞ፤ አሊያም እያደረጋችሁም ንስሐ ተቀብላችሁ ቢሆን መንፈሱ ሙሉ በሙሉ በእናንተ ላይ አቅም ያጣል። በኋላም በዚህ ሰማያዊ ልምምድ ጸንታችሁ እየቆያችሁ ሱባዔ እየያዛችሁ ስለ ወደፊቱ ደግሞ መረጃ ጠይቁ። በምታገኙትም ምሪት እየሄዳችሁና ሥጋና ደሙን በተደጋጋሚ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ በመውሰድ ሙሉ በሙሉ ዲያቢሎሱን እንጥለዋለን። ለመንግሥቱም የበቃን ልጆች እንሆናለን። ምክንያቱም

" በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።"(ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥37)

ማሳሰቢያ፦ ይህ የጸሎት ቤት የመርሃ ግብር ቅደም ተከተል በስርአት መልኩ የሚወሰድ አይደለም። የግል ተሞክሮን ከማካፈል አንፃር፣ መረጃ ከማቀበል አንፃርና መንፈሳዊነትን ከማሳደግ አንፃር የቀረበ መሆኑን ለማሳወቅ እወዳለሁ። ግዴታ ይህንን መንገድ መከተል አለባችሁ፤ ከዚህ የዘለላችሁት አሊያ ቅደም ተከተሉን ያልጠበቃችሁት ተሳስታችኋል የሚል ነገር የለም። እግዚአብሔር የቢሮክራሲ አምላክ አይደለምና የአካሄዳችንን ጥራት አይቶ የሚቀበል አባት አይደለም። በጸሎትና በምስጋና ግዜ ዋናው ከፍቅርና ከእውነት የተነሣ መሆኑ እንጂ በጸሎት አካሄዱ መሠረት አይደለም እግዚአብሔር የሚያስተናግደው።

## ክፍል - 11

### የጸሎተ ሰዓታት ውጊያ

ከመሠረታዊ የአምልኮት ትምህርትና የዲያብሎስ ውጊያ መካከል ቅድሚያ ከሚሰጣቸው መካከል ሰባቱ የጸሎት ግዜያት ናቸው። በነዚህ ግዜያቶች ታዲያ መንበርከክ ማስለመድ እጅግ መልካም የክርስትና አቋሞ እንዲኖረን ያግዘናል። ከዚህ በተጨማሪ በየሦስት ሰዓቱ የምናደርገው ጸሎት መታደሻ ነው። በአካልና በአእምሮ ስንዝል ገብተን በርከክ ብለን ስንወጣ እንታደሳለን። ልክ እንደ ጋራዥ ማለት ነው። በሌላውም ጸጋችን፣ የማስተዋል ጥበባችን፣ በረከትና ረድኤታችን እያደገ ይመጣል።

ከባህሪያችን ውስጥ ባህሪይ ሆኖ ያደፈጠ ርኩስ መንፈስ ታዲያ ይሄንን በየሰዓቱ የመንበረከክ መንፈሳዊ ልምምድ በጣም በጣም ነው የሚጠላው። ምክንያቱም ጸሎት ባደረሳችሁ፣ በሰገዳችሁ፣ በመቁጠሪያ በነረታችሁት ቁጥር እየተቃጠለና ኃይሉ እየደከመበት፣ የጥፋት መንገዱም እየተዘጋበት ስለሚሄድ ነው።

በየጸሎት ሰዓቱ መንበረከኩ ለእናንተ የማይታወቅና የማይገለጥ ትልቅ ጥቅም አለው። ምናልባት መንፈሳዊ ዓይን ቢሰጣችሁ ጸሎት በገባችሁ ቁጥር ምን ያህል ጠላት እንደሚንጨረጨር ብትረዱ ከጸሎት ቤት አትወጡም ነበረ።

የጸሎት ሰዓታት ጠብቀን ለአምልኮት እንዳንቀድም ታዲያ የተደበቀ ጠላት በተጠና አካሄድ፣ በጥበባዊ ስልት፣ በተሰወረ መንገድና በምንም መልኩ በማንጠረጠርው አሠራር ይዋጋናል። ከነዚህ ስልቶቹ መካከል፦

✓ አስቀድሞ ጫና እንዲበዛብን፣ ሥራ እንዲወጥረን፣ በሆነ ፕሮግራም ወጥሮ ግዜያችንን ያስረዋል።

✓ ልክ የጸሎት ሰዓት ሲቃረብ የሆነ ቅርብ ያለ ሰው ወይንም ሌላ ሰው ይለክፈናል። ውኃ ቀጠነ ብሎ እንድንበሳጭ ያደረገናል። ወይንም አስቀድሞ ያስለክፈን ወይ ያጣላን እና ሙሉ ቀን እንዳንጸልይ ደብቶን እየተናደድን እንድንወል ይገፋፋናል።

✓ የጸሎት ሰዓት ላይ ሥልክ ተደውሎ በሆነ እቅድና ፕሮግራም እንድንያዝ ሊያደርግም ይችላል። ወይም ሥልክ ይህቺ ወሬ(chat) የለመድን ከሆነ የጸሎት ሰዓት ላይ ሞቅ ያለ ወሬ እንደምናወራ አስመስሎ ሊያሳየን ይችላል። ወይ የሆነ የቴሌቪዥን አሊያ የራዲዮ ፕሮግራም በጸሎት ግዜያት መዳረሻ ላይ እንዲመስጠንና እንድንዘናጋ ያደርጋል።

✓ እንደ ዓይነጥላ እና መተት አይነት ተዘዋዋሪ መናፍስት ከሆኑ ደግሞ ልክ ጸሎት ልንገባ ስንል ሌላ ሰው ላይ ሄዶ ይቀመጥና እንዲታመም ወይ በሆነ ነገር እንዲጨነቅ ያደርገዋል። በዚህ ምክንያት ትኩረታችንን ሰርቆ እንዳንጸልይ መንገድ ያመቻቻል።

✓ የጸሎት ሰዓት ሲደርስ ድብዛዜ ይለቃል። አንዴ ሕሊና ውስጥ ተቀምጦ አዚም ከሆነ በኋላ በቃ ጸሎት ያስጠላሃል። ሳትጀምረው ይደክምሃል። ወይንም ቀጣዩ የጸሎት ሰዓት ላይ ተነቃቅቼ እገባለሁ እንድትልና ጸሎት እንድትዘል ያደርጋል።

✓ አሊያም አንዳንድ ግዜ ምን ያደርጋል፤ በጸሎት ሰዓት አንዳች የሰውነት ክፍላችን ላይ ሕመም የሚሰማን ከሆነ፤ ቀጣዩ የጸሎት ሰዓት ከመድረሱ አስቀድሞ እንደቀደመው እንደሚያመን አድርጎ ስለሚያሳየን፤ ፍርሃት ተሰምቶን የጸሎት ሰዓት እንድንሸሽ ያደርገናል።

### 11.1) ምን እናድርግ?

"ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው።" (የማቴዎስ ወንጌል 26፥41)

ትጉና ጸልዩ የሚለው ቃል የሚነግረን እዚህኛው ቦታ ላይ መገኘት የሚገባውን የሰዓታተ ጸሎት የዲያቢሎስን ውጊያ በማሸነፉ በኩል ልንሄድበት የሚገባውን አቅጣጫ ነው።

❖ ትጋት የሚባለው መንፈሳዊ ጦር ሊበረታ የሚችለው በተገባ ለአምላክ ያለን ፍቅር ሲጨምር ነው። ጸሎት ማለት ከአምላክ ጋር የመገናኛ ቋንቋ ነው። ስለዚህ ከአምላክ ጋር ለመገናኘትና ግዜያችንን በእርሱ ለማሰባረክ ሁልግዜ መናፈቅና መጓጓት አለብን። አሁን እንዴት ነው ከምንወደው ሰው ጋራ እንኳ ለመገናኘት የምንጓጓ እንሆን እና፤ ከሰማያዊ አምላክ ግን በጸሎት ለመገኘት ያለን የልብ ፍላጎት በጣም የቀዘቀዘና የተልፈሰፈሰ ይሆናል። ስለዚህ ለሰማይና ለምድር አባት ልዑል እግዚአብሔር ያለንን የልብ፣ የነፍስና የአሳብ ፍቅር መልሰን መላልሰን እየፈተሸን ማደስ ያስፈልገናል።

❖ በእጅ የምንይዘው ሥልክ ላይ አሊያ ሰዓት ላይ የማንቂያ መጥሪያ(alaram) መሙላት። ሦስት፣ ስድስት፣ ዘጠኝና ዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ ማንቂያ በማዘጋጀት ለጸሎት የነቃ ሕሊና እንዲኖረን መጣር።

❖ ጸሎት ስንገባ ለቀጣዩ የጸሎት ሰዓትም በምስጋና እና በአምልኮቱ ቦታ ላይ እንድንቀም በቃለ-ኪዳን ጸሎት ሁልግዜ ማሳሰብ።

❖ ጸሎት ሰዓታት መዳረሻ ላይ ምንም ነገር ከማድረግ፣ ከመስማትና ከማየት መቆጠብ። ጸሎቱን ስንጨርስ የሚደርሰው ይደርሳል።

❖ በየጸሎቱ ሰዓት ያደፈጠን ጠላት በቃለ-ኪዳን እያሰሩ በመቁጠሪያ ማቀጥቀጥና በዛው አዳክሞ የአምልኮት ስግደት መስገድ።

"ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።" (ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 4፥6)

## ክፍል - 12

### አጋንንትን ስለማሰር

" እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።" (የሉቃስ ወንጌል 10፥19)

ይህንን ቃል ሰው አይደለም የተናገረው። ዓይኖቹ የፍቅር ጨረር የሚለቁ፣ እጆቹ በቸርነት ኃይል የሚዳብሱ፣ እግሮቹ ወደ ተጨነቁት የሚሄዱ፣ ልቡ በገርነትና በምሕረት የተሞላው፣ የመድኃኒዓለም ቃል ነው። የሚጎዳችሁ የለም እኮ ነው። አስቀድሙና ስታመልኩ፣ ስትሰግዱ፣ ስትጸልዩ ፍቅሩን አስቀድሙ። ታዲያ ያኔ ምን ያሰጋናል? ሰይጣን ስትሰግዱና ስትጸልዩ ምልክት ካሳየ እንግዲያስ እረኛችን እግዚአብሔር የሚያደርገውን እንደምን ያለውን ነው?

ይህንን ብቻውን ማሰብ በራሱ የውስጥ ኃይልን ይሰጣችኋል።

"በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል። " (መዝሙረ ዳዊት 23፥4)

ሰጠኋችሁ ያለው እርግማን አይደለም። ችግር አይደለም። መውደቅን አይደለም። የሰጠን ሥልጣን ነው። ሊያውም በጠላት ኃይል ሁሉ ላይ የሚነግስ።

ኃይል የምንለው መንፈሳዊ ጉልበትን ለመረከብ ጊዜ ያስፈልጋል። ስትሰግዱና ስትጸልዩ ያደፈጠ ዲያቢሎስ የሚረበሸውና የሚበጠብጠው ተመቻችቶ እንዳይቀመጥ እረፍት ስለምትነሱት ነው። በአምልኮ ልምምድ ውስጥ ዲያቢሎስ ሲረብሻችሁ በእውኑ ደስ ይበላችሁ። ምክንያቱም ከውስጣችሁ ቤት ልታስወጡት እየታገላችሁት ነውና።

ክርስቶስ የሰጠንን የሥልጣን ኃይል ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚያድግ እንጂ ታሽጎ እንደተቀመጠ ንብረት በአንዴ የምንቀበለው አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከጊዜ ወደ ጊዜ በበረከትና በጸጋው መገለጥ እያለፈ ከውስጣችን የሚያድግ ጉዳይ ነው።

አጋንንትን ለማሰር የቃል-ኪዳን ጸሎት እናቀርባለን።

ቃል-ኪዳን ማለት ከእግዚአብሔርና ከእግዚአብሔር ቅዱሳን ጋር ቃል የመገባባት ጸሎት ማለት ነው። የፍቅር ጸሎት ነው። የእምነት ጸሎት ነው። አሳልፎ የመስጠት ጸሎት ነው።

#### 12.1) አጋንንትን ለማሰር

☞ የዕለቱን ስግደትና ጸሎት ካደረስን በኋላ ቀባዕ ቅዱስ አንስተን ግንባራችንን 3 ጊዜ በአምሳለ መስቀል አድርገን በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንቀባለን

☞ አንድ እጃችንን የቅዱስ ሚካኤል ስዕል ላይ ሌላውን የቀባነው ግንባራችን ላይ እናደርጋለን

☞ ሊቀ መልአኩን በቃለ ኪዳን ጸሎት እንማጸናለን

በምሳሌ እንደዚህ ብለን፥

<< የእግዚአብሔርን ሕዝብ የምትጠብቅ ታላቁ መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ፥ በሰማይ ታላቅ ሰልፍ በሆነ ጊዜ ከፊት ቀድመህ ዘንዶውንና የጽልመት አለቆቹን እንዳሸነፍክ፤ እንዲሁ በኔም ሕይወት ከፊት ቀደምና በዘመኔ የሚጣሉኝን ርኩሳን በእሳት ዛንጅር እሰርልኝ። ሚካኤል በተሰኘው የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያሳስበውን ስምህን ስጠራ ኃይለ መንፈስ ቅዱስን ላክልኝ። ቅዱስ ሚካኤል ሆይ፥ የቸርነት መልአኩ ሆይ፤ በጸሎቴ ጊዜ የሚረብሸኝን፣ የሚያስታጉለኝንም የሚበረታታብኝን ክፉ መንፈስ አንተ በሰይፍህ ጣልልኝ። የእግዚአብሔር ሕዝብ የምትመራ አንተ አለቃ ሆይ፥ እኔንም ከከበቡኝ የጨለማ ጠላቶቼ መካከል በብርሃኑ መንገድ ምራኝ። በውስጤ

የመሸገን መንፈስ ያየሁትን እንዳያይ ዓይኑን አጨልምበት። የሰማሁትን እንዳይሰማ ጆሮውን ዝጋበት። የማስበውን እንዳያውቅ ወደ ግንባሬ አምጥተህ በመንፈስ ሰንሰለት እሰረው። የእግዚአብሔር አገልጋይ ብርቱው አባቴ ሚካኤል ሆይ፥ በነገድህም ፊት ቀመህ በጸለይህም ጊዜ እኔን ደካማውን አስብ። ሚካኤል ሆይ፤ እንዳትረሳኝ ብዬ በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተማጸንኩህ። ሚካኤል ሆይ፤ ኃይልህንም ኃይሌ አድርገህ ጠላቴን ታርቀው ዘንድ በወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ስም እለምንሃለሁ። ሚካኤል ሆይ፥ ከኃጢአቴም ብዛት እንዳትተወኝ፤ በክፋቴም እንዳትረሳኝ ስለ ስምህ ኪዳንህን አስር ዘንድ በወዳጅህ አጽናኙ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ስም እማለድሃለሁ። ሚካኤል ሆይ፥ በስዕልህ ፊት ተንበርክኬ የምነግርህን ታስብ ዘንድ በእግዚአብሔር ክብር ለነገሱ ቅዱሳን ስም እለምንሃለሁ። ሚካኤል ሆይ፥ ርኩሱ በኔ ላይ እንዳይሰለጥን ሰይፍህን ትጥልበት ዘንድ በቅዱሳን ሐዋሪያት ስም እማልድሃለሁ። አለቃው ሚካኤል ሆይ ከነኔ ተሰለፍ >> (ለሌሎች ቅዱሳንም በተመሳሳይ ሁኔታ በቃል ኪዳን ጸሎት በማሳሰብ መንገር እንችላለን)

☞ አስከትለን የቅዱስ ሚካኤልን ስዕል ምንጣፋችን ላይ አኑረን ግንባራችንን ልክ ሰይፉ ላይ እያስነካን፣ አሊያም የሌሎችን ቅዱሳን ስዕል ወይንም ጸሎት መጽሐፍ ላይ እያስነካን 'ውስጤ የተደበቀ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አብረኸኝ ስገድ' ብለን የአምልኮት እንሰግዳለን።

☞ በመቀጠል ታስሮ እንዲሰግድ የተገደደውን መንፈስ በመለኮተ ስሞችና በቅዱሳን ስም አዘን፤ በመቁጠሪያ እንቀጠቅጣለን፡

**ክፍል - 13**

## የጸሎት ውኃ እና ቅባዕ ዘይት

ከቅዱሳት ስዕለ አድኖ፣ የጸሎት መጽሐፍት፣ መቁጠሪያ በተጨማሪ በጣም አስፈላጊው የጸሎት ቤት ንብረት ቅባዕ ቅዱስ እና የጸሎት ውኃ ነው።

እነዚህ የጸሎት ቤት ንብረቶች በመጀመሪያው ደረጃ በምንባርክበት ግዜ የምንገለገልባቸው የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ ናቸው። ቅባዕ ቅዱስ በተለይ ስዕለ አድኖዎቹን፣ መቁጠሪያውን እና ሌላ መባረክ የሚያስፈልገውን ንብረት የሚባረክበት ቅባት ነው። የጸሎት ውኃ በመጠነኛ እቃ ተቀንሶ የተቀመጠ ከጸሎት ስፍራ ውጪ የማይንቀሳቀስ የቤተክርስቲያን ጸበል ነው።

የጸሎት ውኃ ለምን ይጠቅማል? የጸሎት ውኃ በማለዳው ክፍለ ግዜ ጸሎት ካደረስን በኋላ እየጠጣን ውስጣችንን የምንባርክበት ነው። ሁለተኛ ጸሎት ከማድረጋችን በፊት ግንባራችንን፣ ጀርባችንን፣ እግራችንንና ሕመም የሚሰማን ቦታ ላይ አሸት እናደርግበታለን። በሦስተኛው በቤት ውስጥ ምግብ ስናበስል በተወሰነ መልኩ እንጨምራለን። ሻይም ስናፈላ የተወሰነ እንጨምራለን። የውጪ ከገበያው ጋር ተያይዞ የሚመጣ የቡዳው፣ የነጋዴው፣ የግፈኛው፣ የምቀኛው መንፈስ ከምንበላው ሙብልና ከምንጠጣው መጠጥ ጋር እንዳይቀራኝ ያሸሻዋል። በተጨማሪም ቤተሰብ ውስጥ በመንፈስ ተጠቅቶ ያለውን ሰው ለማገዝ የሚበላውና የሚጠጣው ውስጥ ጸልዮና ጠብ አድርጎ መስጠት የተደባለቀውን መንፈስ ሊረብሸውና ሊገልጠው ይችላል። ቀባ ቅዱስንም መጨመር እንችላለን።

ቅባዕ ሜሮን እና ቅባዕ ቅዱስ ይለያያል። ቅባዕ ሜሮን እንደ ሚስጥረ ቀንዲል ያሉ ሥርአተ ቤተክርስቲያን የሚከናወንበት፣ የቤተክርስቲያን መቅደስ ንዋየ ቅዱስ ንብረቶች የሚባረኩበት፣ ጽላትም ላይ የሚቀባ በካህናት ብቻ የሚደረግ ነው። ቅባዕ ቅዱስ ወይንም ቅባዕ ዘይት ግን ምዕመናን በጸሎት ቤት ብቻ የሚያኖሩት፣ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ውጪ ለሌላ መጠቀም የማይቻል፣ በየቤተክርስቲያናት መደብርና ገዳማት የሚገኝ የጸሎት ቤት ንብረት ነው።

### 13.1) ቅባዕ ቅዱስን በዲያቢሎስ ውጊያ ግዜ እንዴት እንጠቀምበት

ባዘጋጀነው የጸሎት ቤት ዘወትር ከልብ የሆነ ጸሎትና ስግደት በምናደርስበት ግዜ ከሰውነት ውስጥ የተደበቁ ጠላቶች የተለያየ ምልክት ያሳያሉ። በሙሪታዊነት የራስ ምታት፣ የቆሸትና ጨጓራ መቃጠል፣ የወገብና የጀርባ ሕመም፣ ድካም ድካም የማለትና የልብ ምት የመጨመር፣ የሆድ ቁርጠት፣ የፊኛና የማኅጸን መጫን፣ ብሽታና የማጥወልወል ስሜት፣ ቶሎ ቶሎ ማፋሽክና ማልቀስ፣ መንጠራራት፣ በአንድ ግዜ የባህሪይ መለዋወጥ፣ ወደላይ ወደላይ የማለትና የመፍዘዝ ምልክቶችን ይሰጣል።

እንደዚህ ምልክት በሚሰጥበት ግዜ አሁን ምን እናድርግ ወደሚለው ስንመጣ፤ ቅባዕ ቅዱስ እዚህ ጋር ይጠቀመናል።

የሰዓቱን ጸሎትና የአምልኮት ስግደት ከጨረስን በኋላ በፍጹም ማመን ሆነን የምንወደው ቅዱስ ስዕለ አድኖ ፊት የመጽሐፍ መግለጫ ያህል ተጠግተን፤ ቅባዕ ዘይቱን እንዲባርኩልን በቃለ ኪዳን ጸሎት እናሳስባለን። ለምሳሌ፦ ቅዱስ ሚካኤል ምስል ፊት ተጠግተን "በስመ አብ፣ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ አሜን። ታለቁ ኃያል መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ ርዳታህን ላክልኝ። ከጎኔ ተገኝተህ የምጠይቅህን ፈጽምልኝ። በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል ባርከኝ። ቀኝህን አሳርፍብኝ። ውስጣዊ ሕይወቴን ቀድሰው። በምስጋናህም ቦታ ሁሉ በጸሎትህ አስበኝ። ሊቀ መልአክት ቅዱስ ሚካኤል ሆይ፥ የሰማይ እውነተኛ ካህን ነህና፤ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ ይሄንን ቅባት በስመ እግዚአብሔር ባርክልኝ። በስምህም መንፈሳዊ ኃይል ቀድሰው። የእግዚአብሔርን መንፈስና መለኮት አኑርበት። ክብርህን ግለጥበት።" ብለን በመለኮተ ስሞቹ << ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ቅዱስ አዶናይ፣ ቅዱስ ኤልሻዳይ፣ ቅዱስ ያሕዌ፣ ቅዱስ ኢየሱስ፣ ቅዱስ ክርስቶስ፣ ቅዱስ አማኑኤል ስም የተባረከና የተቀደሰ ይሁን>> ሰንል እንባርከዋለን።

ከዚያ ጸሎት ስንጸልይ የሚያቃጥለን፣ ምልክት የሚሰጠን ቦታ ላይ እንቀባዋለን። ሆዳችን ከሆነ ሆዳችንን፣ ጭንቅላታችን ከሆነ ጭንቅላታችንን፣ ዓይናችን ከሆነ ዓይናችን፣ እግራችን ከሆነ እግራችንን እንቀባለን። ጨምድዶ የያዘን ቦታ ላይ፣ ሕመም የሚሰማን ቦታ ላይ፣ የሚያስጨንቀን ቦታ ላይ እንቀባዋለን።

በመቀጠል ከቀባንበት ቦታ "በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውጣና ግንባር ላይ ታሰር" ብለን ግንባራችንን አስከትለን አመሳቅለን ቀብተን እናስረዋለን። የእምነት ጉዳይ እንጂ በቀጥታ ከተደበቀበት ቦታ ወጥቶ ይታሰራል። ከልባችን በስመ ኃያሉ ካዘዝነው አንዳንድ ግዜ እንደሚንቀሳቀስ ነፍሳት ወጥቶ ሲታሰር ሊሰማን ይችላል። ባንሰማውም ከኛ የሚጠበቀው አምነን ማዘዙ ብቻ ነው። ግንባር ላይ ሆኖ ለመታሰር ይገደዳል።

በመቀጠል መቁጠሪያውንም ይህንኑ ቅባት ቀብተን እና ባርከነው "ያደፈጥህ፣ አሳቤን የምትበርዝ፣ መተት፣ ዓይነጥላ፣ የቤተሰብ ዛር፣ ቡዳ፣ ጠቋር፣ ወዘተ..." እያልን በእምነት ስንቀጠቅጠው፤ ተጨማሪ ምልክቶችን እየሰጠን ይሄዳል።

ከዚህ በኋላ ተከታዩ ጉዳይ የሚሆነው ማዳከም ነው። በስግደት፣ በጸሎት፣ በጸበል ጠዋት ማታ ስናሰለቸው መናዘዝ እና የያዘውን መልቀቅ ይጀምራል።

## ክፍል - 14

### ቅዱስ ቁርባን

ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ የሆነው ቁርባን የሚለው ቃል የሱርስት ቃል ሲሆን በቁሙ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መንፈሳዊ አምኃ፣ መስዋት፣ መባዕ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ይቀርብ የነበረው የመስዋዕት ቁርባን፤ ከበግ፣ ከላምና ከተለያዩ የእንስሳት ነበር። በሐዲስ ኪዳን ግን እንስሳት በቤተ መቅደስ ውስጥ ቁርባን(መስዋዕት) ሆነው አይቀርብም፤ መስዋዕት ሁሉ በክርስቶስ ሥጋና ደም ተጠቅሏልና።

ቅዱስ ቁርባን ሕይወት ነው። ቅዱስ ቁርባን የዘላለማዊነት ማኅተም ነው። ቅዱስ ቁርባን የክርስቲያን ኃይል ነው። የጸጋው ምንጭ ነው። የቃልኪዳን ስጦታው ነው። ምርኩዝ ዋሱ ነው። ያለ ቅዱስ ቁርባን ክርስትና ዜሮ ፋርሽ ነው። ክርስትና ክርስቶስነት ነውና። ክርስቶስነት እንኪያስ ሥጋና ደሙን በመቀበል ውስጥ ክርስቶስን መልበስ ነው። ያለ ቅዱስ ቁርባን ሰማያተ መንግሥትን መውረስ አይቻልም። የክርስቶስ በጎች የሚገቡበት የበረቱ በር ቅዱስ ቁርባን ነው። ቅዱስ ቁርባን የትንሣኤ ማጽደቂያው ነው። ያለ ሥጋና ደሙ ሕይወት ማግኘት አይቻልም።

(የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6)

54፤ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።

56፤ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።

#### 14.1) ቅዱስ ቁርባን ለመውሰድ ምን ያስፈልጋል?

ንስሐ ያስፈልጋል። የቅዱስ ቁርባን መሠረታዊ መስፈርት ሰውነትንና ውስጣዊ ሕይወትን ከኃጢአት ማንጻት ነው። ምክንያቱም አዲሱ ወይን የሚሞላው በአዲሱ አቁማዳ ነው። ቅዱስ ቁርባን የሚወሰደው ከኃጢአት በታጠበ ሰውነት ነው። የቃናው ሠርግ ቤት ጋኖች ውኃ ተሞልተው ወይን ከመሆናቸው በፊት የሚቀረው ቅራሪያቸው መደፋት ነበረበት። እነሆ ወይኑ በሕይወታችሁ ውስጥ እንዲሞላ የኃጢአት አተላ ሁሉ መደፋት ያስፈልገዋል።

ከዚህ በዘለለ የዕድሜ ክልል፣ የኑሮ ሁኔታ እና ማኅበራዊ ነገራት ቅዱስ ቁርባንን ከመውሰድ አያግድም። ንስሐ ተቀብሎ ቀኖናውን የጨረሰ ሰው ሁሉ መቁረብ ውዴታው ሳይሆን ግዴታው ነው። ምክንያቱም ያለ ቅዱስ ቁርባን ክርስቲያንነት ሊጸና አይችልም። ክርስቶስ የሌለበት ሕይወትና ኑሮ የክርስቲያን አይደለም። ክርስቶስን ያልተከተለ ጉዞ የክርስትና መንገድ አይደለም። ስለሆነም ያለ ቅዱስ ቁርባን ክርስትና የለም።

ዛሬ ዛሬ በሚያሳዝን አኳኃን ካህናት ጭምር ምዕመኑን ከቅዱስ ቁርባን አርቀውታል። "ቀይ ዕድሜህ ገና ነው፣ ትንሽ ሰከን በል ልትሳሳት ትችላለህ፣ ወጣት ለቁርባን ዝግጁ አይደለም" እያሉ ወጣቱን ማኅበረሰብ ከክርስቶስ ሥጋና ደም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሚያርቁ አባቶች አሉ። በዚህ ምክንያት ትውልዱ ቁርባንን ይፈራል። ሥጋና ደሙን ይሸሻል። በዚህ ሽሽት ውስጥ ታዲያ ዲያቢሎስ የራሱን ወጥመድና መረብ ዘርግቶ የሰው ልጆችን በመጠላለፍ ገና ከማለዳው ጀምሮ ትውልዱን በመያዝ ብዙ ውድመቶችን እንደ ተናጠልም እንደጋራም አድርሶ በብዙ አቅጣጫዎች ላይ አክስሮን ቁጭ አለ።

## 14.2) ቅዱስ ቁርባንን ለምን እንወስዳለን?

## 14.3) የቅዱስ ቁርባን 7 ጥቅሞች

1. **አንደኛ ኃጢያትን ለማስተሰረይ፡–** ኃጢያት ተሰረየ ማለት ካንተና ከልጆችህ፤ ከቤትና ከኑሮህ፤ ከታሪክህና ከዘመንህ ሁሉ ተወገደ ማለት ነው። ኃጢያት ተሰረየ ማለት በሚቀጥለው ዘመን ላይ ሊያደርስ የሚችለው ጉዳትና እንቅፋት ቀመ ማለት ነው። የዲያብሎስ ሽምቅ ውግያና ስልቱ ሁሉ በሕይወትህ ያዘጋጀው መዝገብ ፈረሰ ማለት ነው።

2. **ሁለተኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ለሕይወታችን አስፈላጊነት፡–** ሁለተኛ እና በጣም ትልቁ በሕይወታችን ውስጥ ፍቅር እንዲኖር የክርስቶስ ሥጋና ደም ያስፈልገናል። ፍቅር እንዲኖር። እግዚአብሔር ፍቅር ነው የሚል ቃል በዮሐንስ መልዕክት ላይ ታገኛለችሁ። እግዚአብሔር ምንድ ነው? ፍቅር ነው። ታድያ ከእርሱ ጋር እርቅ ሳናደርግ፤ በሰውነታችን ውስጥ ስፍራ ሳይይዝ፤ በባህሪያችን ውስጥ ሳይገባ፤ በሚስጥረ መለኮት የሰጠው ሥጋና ደሙን ሳንቀበል አሁን ከዚህ ትውልድ ፍቅር ይጠበቃል ወይ? እንዴት ይሆናል? እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ፍቅር ሲጠፋ የክርስቶስ ሥጋና ደም ያስፈልገናል። እንዲህ ብለን ወደሱ እንጠጋለን "አቤቱ ጌታ ሆይ ፍቅር ከህይወቴ ጠፍቷል።" እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ንቁ የሚለው በዚህም ጭምር ላይ ነው። ከቤተሰብህ ፍቅር ሲጠፋ <ጌታ ሆይ ፍቅር ሁነኝ> ማለት አለብህ። "በውስጤ ውስጥ እደር ባህርያቴን ለውጠው፤ ሰማያዊ የሆነ ስጦታህን አካፍለኝ፤ የቸርነትህ ጸጋ ከኔ ጋር ይሁን፤ ሁሉ ግዜ በሃሳብህ ባርከኝ፤ ፍቅርህ ከሁሉ በላይ የሕይወቴ ፈር ይሁን" ብለህ ቅዱስ ቁርባን ስትወስድ ፍቅሩን ይመልስልሃል። በፍቅርህ ውስጥ ጠላት የሆነውን ኃይል ከሕይወትህ ያስወግደዋል። በዚህ ግዜ እንግዲህ ለአገርህም፣ለወገንህም፣ ለህዝብህም፣ ለጎረቤትህም፣ ለጠባይህም፣ ለቤትህም፣ ለገንዘብህም ፍቅር ትሆናለህ ማለት ነው። ገንዘብ አንተ አፍቅረኸው ሳይሆን ገንዘብ አንተን አፍቅሮ ወደ አንተ ይመጣል። ኑሮ አንተ አፍቅረኸው ሳይሆን ኑሮ አንተን አፍቅሮ ወደ አንተ ይመጣል። እንጀራ አንተ ወደኸው ሳይሆን እንጀራው አንተን ወዶ ወደ አንተ ይመጣል። ግዜ አንተ ወደኸው፤ አንተ አቅደኸው ሳይሆን ግዜው አንተን ለመርዳት ወደ አንተ ይመጣል። በእያንዳንዱ ግንኙነቶችም ውስጥ ሰማያዊ ፍቅር እስካለህ ድረስ ተፈጥሮዎች ያገለግሉሃል። እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን። እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

3. **ሦስተኛ ቅዱስ ቁርባን የሚያስፈልገን ሰውነታችን ሲከብደን ነው፡–** ሰውነት ሲከብድ፤ መጫን ሲጀምር፤ ውስጣዊ ህይወትህ መረጋጋት ሲያቅተው በዚህ ጊዜ ማቴዎስ ወንጌል ላይ የተናገረው ቃል ትዝ ሊለን ይገባል። የማቴዎስ ወንጌል

ምዕራፍ 11 መጨረሻው ላይ እንዲህ ይላል ‹‹እናንተ ሸክም የከበዳችሁ ወደኔ ኑ››። ምን የከበዳችሁ? ሸክም። የግዜ ሸክም፣ የኑሮ ሸክም፣ የትውልድ ሸክም፣ የዓመታትን ሸክም። ስንት ዓመታቶች አልፈው፤ ዛሬ እየከበደን እየከበደን የመጣውን ሸክማችንን ማን ይቻለው? እኛ ነን የምችለው? ምድራቱ ነች የምትችለው? ኑሯችን ነው የሚችለው? ገንዘባችን ነው የሚችለው? ማን ነው የሚችለው?

በእርግጥ ተናገሩ ብንባል የፈጠረን አምላክ ይችልልናል ነው የምንለው። በእውነታና በሕይወት ውስጥ ባለው ትርጉም ውስጥ ግን የሚታይ ምላሽ የለንም። ስለዚህ በሽለቀ ውስጥ ሆነን ሰማያዊ ነገር አልታይ አለን። ሲከብደን ቅዱስ ቁርባን ያስፈልገናል። ምን ማለት ነው እንግዲህ? ሽክም ማራቀያ ነው ማለት ነው።

4. አራተኛ በረከት ከሕይወታችን ሲጠፋ፡— በረከት ከሕይወታችን ሲጠፋ የበረከት አምላክ ሕይወታችንና ኑሯችን ውስጥ እንዲኖር ቅዱስ ቁርባን ያስፈልገናል። በረከት ከምናችን ሲጠፋ? ከህይወታችን፣ ከኑሯችንና ከቤተሰባችን ሲጠፋ። ያኔ አንድ ነገር ገብተዋል ማለት ነው። የበረከት ጠላት በዙሪያችን አለ ማለት ነው። እንኪያሳ በበረከት ጎዳና ውስጥ እንጀራን ለብዙ ሺ ህዝብ የመገበ አምላክ ለኛም ሊሰጠን እንደሚችል ልቦናችን ማሳመን መቻል አለብን። ስለዚህ "ጌታ ሆይ አንተ የበረከት ንጉሥ ነህ የጎደለውን በረከቴ አንተ ሙላልኝ፤ የበረከት ጠላትን ኃይል አርቅልኝ" ብለን እሱ ተማፅነን ቅዱስ ቁርባን ስንወስድ በረከታችን ይመለሳል።

5• አምስተኛ መልካምና ጥሩ ዘር ለማግኘት፡— መልካም ትውልድ ለማፍራት ቅዱስ ቁርባን ያስፈልጋል። መልካም ትውልድ፤ የእግዚአብሔር የሆነ ትውልድ፤ የሰማይ አምላክ የሆነ ትውልድ። ዛሬ በአብዛኛው ከዚህ መንፈሳዊ በረከት ርቆ የተወለደው ቃልቻ ሆነ፤ ጠንቋይ ሆነ፤ መተተኛ ሆነ። ከዛም ደግሞ አልፎ ተርፎ እንዲሁም የተወለደው የመተተኞች፣ የአስማተኞች መንፈስ መኖርያ ሆነ፤ የዛርና የውቃቢ መጫወቻ ሆነ፤ የክፉ ባህርይና የክፉ ጠባይ መጫወቻ ሆነ። ይህ ሁሉ ከቤተሰብ መንፈሳዊ ትከሻ አንፃር ያለው ጉዳት ነው። አብዛኛው ወላጅ እያወረሰን ያለው ሰማያዊ ነገርን ሳይሆን፤ ሰማያዊ ስጦታ ሳይሆን፤ ክፋውን ነው የምናወርሰው። ይህንን ውርስ ለመከላከል ለልጆች ቅዱስ ቁርባን ሊወሰድላቸው ይገባል።

በሁለት አይነት መንገድ፦

♦ አንደኛ ከመወለዳቸው በፊት ቤተሰቦች ቅዱስ ቁርባን ለሚወለዱት ገና ለሚፀነሱት አስበው ቅዱስ ቁርባን መውሰድ አለባቸው። ☞ ክፉ መንፈስ አብሯቸው ከማኅጸን ጀምሮ እንዳይወለድ

♦♦ ሁለተኛ ከተወለዱ በኋላ ለልጆቻቸው ቅዱስ ቁርባን መውሰድ የሕይወት መርሃቸው ማድረግ አለባቸው። ☞ ሕይወታቸውን ከማለዳው ክርስቶስ እንዲመራው

6• ስድስተኛ ቅዱስ ቁርባን የሚወሰደው የእግዚአብሔርን መልስ ስንፈልግ ፡- ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ስትጀምሩ

በፍጹም ከሰው ልጅ ጠባይና ባህሪይ ጋር አትስማሙም። ስለዚህ ብቸኝነት ይሰማቹሃል። በዚህ ግዜ "ጌታ ሆይ ዓለሙ ከኔ ሸሽተዋል አንተ ከእኔ ጋር ሁን" ማለት እንጀምራለን። ልክ በዚህ ወቅት የሕይወት ደስታ እና እርካታ አንድ ሺህ ሰው ከከበበን ይልቅ ለብቻችን ከክርስቶስ ጋር የምንኖረው ኑሮ ያረካል። ያ አንድ ሺህ ሰው ቢከብህ እየተቸ፤ በገሪጥ አፉን እያጣመመ፤ ዓይኑን እያጨነቀረ ነው የሚያይህ። እግዚአብሔር ግን በብቸኝነት ውስጥ ብርሃን ይሰጥሃል። ይሄ ነው የሱ ልዩ ሞገስ። መልሱንም በራእይ ወይም በህልም ስንጠብቅ ተገቢ በሆነ ጊዜና ሰዓት እግዚአብሔር ይሰጠናል። ውስጣችን መቀደስ ሲጀምር ከውጪ ያለውን እግዚአብሔር መሪ ይሆናል ማለት ነው። እያሱ ህዝቡን ሲመራ፤ በመጽሐፈ እያሱ ምዕራፍ አንድ ላይ አንድ ታላቅ ድምፅ እንሰማለን እንዲህ ሲል ‹‹በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ማንም አይቋቋምህም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ።››

በቃ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ማንም አይቋቋምህም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ የሚለውን ድምፅ የሰማው ማን ነው? እያሱ ነው። የእስራኤልን ህዝብ ወደ ምድረ ርስት ለመውሰድ በሚያደርገው ጉዞ ውስጥ፤ የርስት ባለቤቶች እንዲሆኑ ለማድረግ ባደረገው ጉዞ ውስጥ፤ ማንም አይቋቋምህም የሚለውን ድምፅ በሕይወቱ ውስጥ እግዚአብሔር ሰጠው። እኛ የምንወርሰው ነገር አሁን ምን አለ?። በመሠረቱ እኮ የእግዚአብሔር ህዝብ መስጠት እንጂ፤ እየሰጠ የሚሄድ እንጂ እያጣ፤ እየደኸየ የሚሄድ አይደለም። እኛ ግን እያጣን፤ እየደኸየን መጣን። ውስጣችን መጀመርያ እግዚአብሔርን አጣ። ከዛ በኋላ በዓለም ላይ ባለው ነገር ላይ ምንም ባለቤትነትን አጣን። ለማንኛውም ነገር ቅጥረኞች ሆንን። ከሁሉም ደግሞ የሚገርመው እንጀራ በባህሪው ከነክፋቱ፤ ከነተንኮሉ፤ ከነምቀኝነቱ ገዛን። እግዚአብሔር የሌለበት ስፍራ እንዲህ ይሆናል። እና ሲከብደን፣ ሲጫነን፤ በአከባቢ፣ በጎረቤት፣ በሀገር ሁሉ ላይ ችግሮች ሲመጡ፤ የእግዚአብሔርን መልስ ለማግኘት ቅዱስ ቁርባን ይወሰዳል ማለት ነው። ከዛ በኋላ ችግራችንን ያስወግዳል የሰማይ አባታችን።

7• ሰባተኛ ስለዘለዓለም ሕይወት ቅዱስ ቁርባን ይወሰዳል፡— ስለምን ይወሰዳል? ስለዘለዓለም ሕይወት። የዘለዓለም ሕይወት አለህ ማለት ደግሞ ይሄ አጥፊው መንፈስ በሕይወትህ ውስጥ ስፍራ የለውም። አንተ የዘለዓለም እንጂ የግዜዎች አይደለህም። ዛሬ በየግዜው

ራሳችንን እያገለባበጥን፤ ኑሯችንን ሲገለባበጥ፣ ጠባያችንን ሲገለባበጥ፣ ህሊናችንን ሲገለባበጥ፣ አመላችን ሲገለባበጥ። እንዴት ነው? እየተገለባበጥን እስከ መቼ ነው? ራሳችንን ለማግኘት ለምን አልቻልንም? ሊቀይ የሚችለው ለምን ማግኘት አልቻልንም?

የዘለዓለም ሕይወት ከውስጥህ ሲወጣ፤ የሚጠብቅህ ነገር ቢኖር እንዲሁ ትርኪ ሚርኪ የሆነ የመንደር ኑሮ ነው። የመንደር ኑሮ፤ የግዜ ኑሮ፤ የሰዓት ኑሮ። ግዜዎች ሲወድቁ አብረህ ትወድቃለህ፤ ግዜዎች ሲጠፉ አብረህ ትጠፋለህ፤ ግዜዎች ሲያርፉ አብረህ ታርፋለህ፤ ግዜዎች ሲሰደዱ አብረህ ትሰደዳለህ።

እንዴት ይሆናል ይሄ? ክርስትያኖች በሰማይ አምላክ ዘንድ ባለ በዘለዓለማዊ ሕይወት መያዝ አለባቸው። እና ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወት ቅዱስ ቁርባን ይወሰዳል ማለት ነው።

## ወስብሐት ለእግዚአብሔር

### ወለወላዲቱ ድንግል

### ወለመስቀሉ ክቡር

አስጀምሮ ላስፈጸመን የሰማዩ አባት ልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይግባው አሜን

የእግዚአብሔር ምኅረት ከሁላችን ጋር ይሁን።

"የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።" (ወደ ሮሜ ሰዎች 16: ፥20)

## ጸባኦት ይከተላችሁ

ከመምህር ግርማ ተማሪ ናትናኤል